ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the source of the Blue Nile



# ናይል
# THE NILE

ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 8፣ መስከረም 2008

## የተመጣጠነ ምግብ በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሊ ዳምጤ (ዶ/ር)

## መረጃና የመረጃ ምንጮች ቁማር

ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)

## ዕልቅናና መሪነት

አለባቸው አስፋው

## The Need to Inspire Civic Virtue and Build Good Moral Character Traits in the Young Generation of Ethiopia

Chalachew Tarekegne

## የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

በፈታሒ በቃሉ





2ተኛው አለም አቀፍ የአዝማሪ አውደጥናት "አዝማሪ ከየት ወደ የት" በሚል መሪ ቃል በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ሲካሄድ





International conference on Tropical lakes 'TROPILAKES 2015' held at BDU

"የመምህራን የምርምር ተሳትፎ የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ አለበት"

አቶ ባየህ አበራ ገጽ 8

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ2007 ዓ.ም ምርጥ ተመራማሪዎች ገጽ 15

Fresh Students' welcoming ceremony of 2008 E.C. academic year (photo gallery)

page 16

እውነትን መፈለግና ስሴሳው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


# ናይል ጋዜጣ

**በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**
**የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል**
**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**



**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
አቶ አማረ ካሳው
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ:-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ
ቃለአብ ሞላ

**ግራፊክስና ሌይአውት:-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች:-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቴ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች:-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
አለባቸው አስፋው
ቻላቸው ታረቀኝ
የኑስ ኑሬ
ስትክልት ዳኛው

**ፎቶ አንሺዎች:-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ:-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ
ፋንታነሽ ላቀው

**ትራንስፖርት:-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች:-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ



ስልክ:- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# እንኳን ደህና መጣችሁ!

አዲስ አመት የብዙ ጉዳዮች መጀመሪያ የአዲስ ምዕራፍ መክፈቻ ነው፡፡ ለተማሪ ደግሞ የክረምት ጊዜውን ከቤተሰቦቹ ጋር ያሳለፈ ወደ ትምህርት ገበታው የሚመለስበት አዲሶቹደግሞ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የሚዛወሩበት የሽግግርና የለውጥ ወቅት ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲያችን በዓመቱ መጀመሪያ ነባር ተማሪዎችን ከእረፍት ከተግባራዊ ልምምድ የሚቀበልበት፡፡ አዲሶቹን እንኳን ደህና መጣችሁ የሚልበት ወሳኝ ክስተት ነው፡፡

በያዝነው ዓመት ከሌሎች የዓመቱ ዝግጅቶች በተጨማሪ አዲስ ተማሪዎች በቆይታቸው ማድረግ ያለባቸውና መከተል የሚገባቸውን የሕይወት መርህና የለውጥና የመሻሻል መንገዶችን በማሳየት መሆኑ ከሌሎች ጊዜዎች ሁሉ ልዩ ትዝታን በሚያስቀር መልኩ ባማረና በደመቀ የሙዚቃ ድግስ መከናወኑ ለየት ያደርገዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን ሁሌም መረጃ እውቀት እውቀት ደግሞ ኃይል መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በትክክለኛና ተጨባጭ መረጃዎች በመያዝ ሕይወታቸውን በስኬት እንዲያጠናቅቁ ይሰራል፡፡ ይህን ተግባሩንም አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ አዲስ ተማሪዎችም ሙሉ የትምህርት ጊዜያችሁን በትምህርትና በትምህርት ብቻ በማዋል የስኬታማዎችን መንገድ ብቻ እንድትከተሉ መልዕክታችን ነው፡፡ በቆይታችሁም የስኬትን ጉዳና በመረማመድ ወደተሻለ የሕይወት ከፍታ እንድትሸጋገሩ ዩኒቨርሲቲው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንደማይለያችሁ እናረጋግጣለን፡፡

በድጋሚ እንኳን ደህና መጣችሁ ቆይታችሁ በስኬት የታጀበ እንዲሆን የናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ምኞቱን ይገልፃል፡፡

## እውነትን መፈለግና ስሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

### ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን
የተለያዩ ጹህፎች፣ ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች፣ የካርቱን ስእሎች፣ ቀልድ፣ ግጥም እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

## ቁልፍ መልዕክት

# የተመጣጠነ ምግብ በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

የተመጣጠነ ምግብ እንደ ተመጋቢው ባህሪ፣ ዕድሜና አካባቢ የሚወሰን ነው፡፡ ስለተመጣጠነ ምግብ ሲነሳ የሰው ልጆችንና ሌሎች እንስሳትን የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉም በየፊናቸው የተመጣጠነ ምግብ ይሻሉ፡፡ በዚህ ጽሑፍ የተመጣጠነ ምግብ ከህገራችን ህዝቦች ጋር በማስተሳሰር በማቅረብ በራዕይ ጥበብ 2017 ይህ ዘርፍ እንዴት እንደሚታይ ይገለፃል፡፡ በዚህም መሠረት የተመጣጠነ ምግብ የሀገራችን ዜጎች እንዲያገኙ በምርምር፣ በማስተማርና በማህበረሰብ አገልግሎት መስራት የሚገባንን ቁልፍ ነገሮች ለይተን እንድንሰራ ያግዛል የሚል እሳቤ አለው፡፡

አንድ የሰብል ዘር በሚገባ በቅሎ፣ አድጎና አፍርቶ ጥሩ ምርት ለመስጠት ጥሩ ዘር መሆንን፣ ሁሉም ንጥረት ነገሮች ያሉበትና በቂ ውሃ ያለው አፈር ላይ መዘራትንና በዕድገት ጊዜም ተፈላጊውን ብርሃንና ንጥረ ነገሮች ይፈልጋል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሲጓደሉ እንደ ጉድለቱ መጠን የመቀጨጭ፣ በቂ ፍሬ ያለመሰጠት ሁኔታዎች ይከሰታሉ፡፡ በተለይ ወሳኝ በሆኑት የዕድገት ምዕራፎች ላይ የሚፈለጉትን ንጥረ ነገሮች ያላገኘ ከሆነ ልናስተካክል በማንችልበት ሁኔታ ምርቱ ሊቀንስ ወይም ምንም ምርት ላያስገኝ ይችላል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የሰው ልጅም ጤነኛና አምራች እንዲሆን ዘሩ የሚያድግበት ማህፀን፣ በህፃንነቱ የሚመገበው የእናት ወተት፣ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት የተመገበው ምግብና እናቱም የሚመገቡት ምግብ ጤነኛና አምራች ዜጋ እንዲሆን የሚወስኑ ነገሮች ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት የሚፈለጉትን ንጥረ ነገሮች በእናትዬዋም በኩል ሆነ በቀጥታ ህፃኑ ካላገኘ ኋላ ልናስተካክለው የማንችል የአካልም ሆነ የስነ አእምሮ ውስንነቶት ይገጥማሉ፡፡ ታዲያ ይህን ወሳኝ ጉዳይ እንዴት ነው የምናየው? በየቀኑ ውሏችን ይህን የግብዓትና የውጤት ግንኙነት በሚገባ ተረድተን እየሠራን ነው ወይ? የመሳሰሉት ጥያቄዎችን በማንሳት ስናየው ብዙ መስራት እንዳለብን ግልጽ ነው፡፡ ያልተመጣጠነ ምግብ ከተመገበች እናትና ኋላም በህፃን ዕድሜ ተፈላጊ ንጥረ ነገሮችን ያላገኘ ህፃን እንደሚቀነጭር ይታወቃል፡፡ የህፃናት መቀንጨር የሚከሰትበት ሁኔታ በርካታ ነው፡፡ የችግሩ ምክንያቶች በዋናነት ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛውና ትልቁ ምክንያት የተመጣጠነ ምግብ ለእናቶችና ህፃት መመገብ ያለውን ትልቅ ፋይዳ ተረድቶ በተግባር ያለማዋል ችግር ነው፡፡ በትምህርት ደረጃ የተመጣጠነ ምግብ መመገብ በተለያዩ ደረጃዎች ቢሰጥም ትምህርትን የህይወት መመሪያ ከማድረግ ይልቅ እንዲሁ ለንግግርና ፈተና ለማለፍ የመጠቀም ባህል በመኖሩ የተነሣ የሚከሰት ችግር ነው፡፡ አትክልትና ፍራፍሬ መመገብ የሚሰጠውን ጥቅም የተነገረው ወይም እንዲማር የተደረገ ሰው መረጃውን እንዲሁ የመያዝ እንጂ ከራስ አመጋገብ ጋር በማስተሳሰር በተግባር ለመለወጥ የምናረገው ጥረት ትንሽ በመሆኑ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲያችን ይህን ሁኔታ ለመለወጥ ሊረባረብ ይገባል፡፡ በተግባር የሚገለጽ ዕውቀትና ክህሎት ጥበብ ይሆናልና ዜጎች ጥበበኛ እንዲሆኑ መስራት ይገባናል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት የማጣት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ችግር ዕውቀቱና ፍላጎቱ ኖሮ በተግባር ለመፈፀም የሚያስችል ሀብት አለመኖርን ያቅፋል፡፡ ዩኒቨርሲቲያችን የተለያዩ የአሠራር ዘዴዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሀብት እጥረቱን ለመቅረፍ መፈፀም የምንችላቸው ተግባሮች ብዙ ናቸው፡፡

የአንድ ሀገር ልማት በወሳኝነት የሚገለፀው በሰው ሀይል ልማት ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ የተመለከተው የሰው ሀይል ልማት በወሳኝነት የሚተገበረው የተመጣጠነ ምግብ አግኝተው እንዲያድጉ በማድረግ የሚጀመር መሆኑን ነው፡፡ በዚህ የመጀመሪያ ወሳኝ ስራ ላይ ያልተሳካ ሁኔታ ካለ በቀጣይነት የሚሰሩ የአቅም ግንባታ ስራዎች ውጤታማ አይሆኑም፡፡ እነዚህ የአቅም ግንባታ ስራዎች የሚጠይቁትና የሚመሰረቱበት ቅድመ ሁኔታ የተመጣጠነ ምግብ በመመገብ ያደገ አእምሮን ነው፡፡ ይህ በሌለበት ሁኔታ የምንሠራው የአቅም ግንባታ ስራ ተራራ የመግፋት አይነት ነው፡፡ ምንም ውጤት የሌለው ይሆናል፡፡

ስለሆነም ወላጆች፣ ትምህርት ቤቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በትምህርት ላይ ከሚሰጡት ትኩረት በበለጠ ለህፃናትና ለእናቶች አመጋገብ ሊሰጡ ይገባል፡፡ የተመጣጠነ ምግብ ተመግበዋል ለማለት በየቀኑ የሐይል ሰጪ፣ የፕሮቲን፣ የተከላካይና የቫይታሚን ስብጥሩን እያሰሉ መመገብን ያቅፋል፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017 እነዚህን ከላይ የተቀመጡ እሳቤዎችን በመያዝ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፎች በማካተት እንዲሠራ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡ በዚህም መሠረት ተረባርበን ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ የመመገብ ባህላቸው እንዲጎለብትና የማግኘት አቅማቸውንም ለማሳደግ በጋራ እንስራ፡፡

**ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!**

# አበይት ዜናዎች...

## “አዝማሪ ከየት ወደ የት?” በሚል ርዕስ ዓውደ ጥናት ተካሄደ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዓባይ የባሕልና ልማት ጥናትና ምርምር ማዕከል “አዝማሪ ከየት ወደ የት?” በሚል ርዕስ ሁለተኛውን ዓለም አቀፍ ዓውደ ጥናት አካሄደ፡፡ የማዕከሉ ዳይሬክተር ዶ/ር ሙሉቀን አንዱዓለም ለእንግዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታት አስተላልፈው ባሕል ሰፊ ፅንሰ ሃሳቦችን አጠቃሎ የያዘና ማንነትን አጉልቶ የሚያሳይ በመሆኑ ማዕከሉ የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ ሀገር በቀል እውቀትን በመፈለግ፣ በማጥናትና በመመራመር ከውጤቱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሳይንሳዊ ግብዓቶችን ለማስገኘት ጠንክሮ እየሠራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ከሀገር በቀል እሴቶች መካከል የአዝማሪነት ሙያ አንዱ ሲሆን ለረጅም ዘመናት በተለያዩ ጊዜና ቦታዎች ማህበረሰቡን እያዝናና በግጥሙ ቁምነገር እያስጨበጠ ቢቆይም ተገቢው ትኩረት ስላልተሰጠው ለወደፊት በጥናት ተደግፎ ዕውቅናን ከተጎናፀፉ ሀገር አቀፍም ሆኑ ዓለም አቀፍ ሙያዎች ተርታ እንዲሰለፍና ለአዝማሪዎችም ተገቢውን ክብር መስጠት እንዲቻል ታልሞ የተዘጋጀ ዓውደ ጥናት መሆኑን ዶ/ር ሙሉቀን ገልጸዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ አዝማሪ በሚያዜመው ዜማና በሚገጥመው ግጥም ማህበረሰቡን አንድ የማድረግ አቅም እንዳለው ተናግረው ዩኒቨርሲቲው አገራዊና አካባቢያዊ እውቀትና ክህሎትን የማዳበር ተልዕኮ ስላለው የአዝማሪዎች ሙያ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሚና ያለው መሆኑን ለማስተዋወቅ እየሰራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

የዓውደ ጥናቱ የክብር እንግዳ የኢፌዲሪ ባሕልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሙሉጌታ ሰይድ የአዝማሪነት ሙያን ለማዳበር ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ እያደረገ ያለውን ሥራ አድንቀው ባህልን ለማዳበር አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን ግጥሞች፣ ዜማዎች እንዲሁም የባህል ሙዚቃ መሳሪዎች ታሪካዊ አመጣጥና በየዘመኑ ያለፉበትን ሂደት ማጥናት አስፈላጊና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው አክለውም ዩኒቨርሲቲው ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ባህላዊ ዘፈኖችና የሙዚቃ መሳሪያዎች በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ ዘንድ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

በዓውደ ጥናቱ ወቅት ስለ አዝማሪ ግጥሞች ስለ አዝማሪ ግጥሞች የተፃፉና የተናገሩ ትውፊታዊና ታሪካዊ ፁሑፎች በሙሁራን ትንታኔአቸው የቀረበ ሲሆን አዝማሪ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ጥበብ ሲሆን አመጣጡ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ተገልጾ ‹‹አዝማሪ ማለት ዘመረ፣ አዘመረ›› ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ መሆኑን እንዲሁም ዘፍኖ አዘፈነ እንደማለት መሆኑ በጥናቱ አቅራቢዎች ተገልጿል፡፡

በዓውደ ጥናቱ ላይ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር የተውጣጡ ምሁራን፣ ታዋቂ የሙዚቃ ባለሙያዎች፣ የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች፣ አዝማሪዎችና የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን በርካታ ተመራማሪዎች ጥናታዊ ጽሁፍ ለውይይት አቅርበዋል፡፡ የተለያዩ አዝማሪዎች አዝናኝና መልዕክት አዛል የሙዚቃ ዝግጅትም አቅርበዋል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው ለአዲስ ተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መርሃ ግብር አዘጋጀ

በአበባ ሃብቱ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለ2008 ዓ.ም አዲስ ተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መርኃ ግብር አዘጋጀ፡፡ በመርኃ ግብሩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ የዩኒቨርሲቲ ህይወት ከቤተሰብ አስተዳደር ወጥታችሁ ብላችሁ ራሳችሁን ልታስተዳድሩ የመጀመሪያውን ምዕራፍ የምትጀምሩበት እርምጃ በመሆኑ ይህን ኃላፊነት በርትታችሁ በመሥራት ብቁ ዜጋ መሆን እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር ፍቅረሰላም አክለውም ብዙ አዲስ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲውን ድህረ ገፅ በመጎብኘት ስለ ዩኒቨርሲቲው መረጃ ማግኘት እንደቻሉ ጠቁመው የዩኒቨርሲቲያችን የመረጃ መረብ በመጠቀም ስለ መማር ማስተማር ሂደት፣ የምርጥ ተማሪዎች፣ መምህራን እና ተመራማሪዎች ተሞክሮ እና በአጠቃላይ ስለ ዩኒቨርሲቲው ሙሉ መረጃ ማግኘት እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

በመረኃ ግብሩ ላይ የተገኙት የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በተለያዩ ቋንቋዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው የተቀበለውን አደራ እንደሚወጣ ቃል ገብተዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ አክለውም ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው የዩኒቨርሲቲውን ህግና ደንብ አክብረው ጠንካራና ሀገር ተረካቢ ኮከብ ተማሪዎች እንዲሆኑ ምክራቸውን ለግሰው ቀሪው የትምህርት ጊዜያቸው ስኬታማ እንዲሆን መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2007 ዓ.ም በከፍተኛ ማዕረግ የተመረቀችው ወ/ት ትዕግስት ፍቅረማርያም አዲስ ለገቡ ተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ካስተላለፈች በኋላ ተማሪዎቹ የዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ስኬታማ እንዲሆን እኔ ማድረግ እችላለሁ የሚል ጠንካራ አቋም እንዲኖራቸውና ውጤታማ እንዲሆኑ የራስዋን የሕይወት ተሞክሮ አካፍላለች፡፡

# Freshman Memories

Yenus Nurie (Department of English Language and Literature)

The sweetest part of students' life in campus - freshman year, completely keeps them busy with exploring new experiences and new friends. It is also embarrassing as they spend their life without parents, and hence it gives them the first opportunity to examine the new life of freedom. Nevertheless, no matter how hard it may be, it is incredible to think what a lovely time they have had in the long freshman year that doesn't seem to an end. Thus, the purpose of this paper is to illuminate few of the most unforgettable freshman experiences that stay in mind of everyone.

Imagine a typical university freshman shambling across various parts of a campus for the first time in his/her life. They do not know what to expect, whom to see, or where to find the registrar, cafeteria or their department. They know no one in the campus which is filled with people just as confused as them. Above all, imagine someone who brought up in a small rural village decides to live in a giant city with skyrocketing buildings that seem to touch the sky.

At the beginning, it is hard for many boys and girls to imagine what campus life would really look like. They may be unable to see themselves living far away in a different town, taking much harder college courses, and struggling to be able to survive. They are frantically agitated to consult people who are not concerned with, hurried and confused with the completely unusual behaviors and philosophies and cultures of the new friends in the campus.

When most of freshman students imagined college, no doubt they would be terrified. They might have been frustrated that they would not fit in, or they would not be able to make friends. Thinking that they will be drawn into the huge personal responsibility, new comers are often corroded by fear.

All they wanted might have been to stay in their little town or village and to stay with their parents and friends. Engulfed by the titanic mismatch between their expectations and the new realities, some of them may even dress improperly to express their feelings and are often observed heading towards outside their campuses. Having departed from their families, freshman students are usually terrified by nightmare and are easily deluded due to temporary and physical satisfactions. Had they known that it was not long lasting paradoxes, they wouldn't have awaited for their academic failure. Thus, it is essential that the new generations should be mindful of the needs of being tolerant in passing the storms until they come to success. Sometimes, it is not surprising to get prank calls from senior students hazing freshman students as the situation and the sudden fear of the new environment leave no room for them to rekindle their life abruptly.

Every day, they meet some events new, or someone strange who may be a new friend, or teacher. Nevertheless, as times go on, the fool's circle starts to be closed. They eventually learn that life can be handled if they get endured. Apart from confronting these challenges;

continued on page 6

## የኔ ሃሳብ

# ዕልቅናና መሪነት

አለባቸው አስፋው (ከቢዝነስና ኢኮኖሚክስ)

የሠው ልጅ በተፈጥሮው አለቃ መሆንን ይሻል። ነገር ግን ደግሞ አለቃ እንዲኖረው አይፈልግም። የፈረንጆቹን ትንታኔ ትተን በኛ አተያይ አለቃነት ከማዘዝ፣ ከማሰራት፣ በሃብት ላይ ያለተቆጪ ከመወሰን አንዳንዴም ‘‘ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ’’ን ከመተግበር አኳያ የሚታይ ነው። አለቃችሁ ማነው ሲሉን በአዕምሯችን የሚመጣው ስናረፍድ የሚቆጣን፣ ስንቀር ያልሰራችሁበት አይከፈልም የሚለን (አሁን አሁን ካለ ነው)፣ የመ/ቤታችንን ሃብት ወደግራና ቀኝ ለማድረግ ስልጣን የተሰጠውን፣ በተለይ እኛን ለማረቅ የወጡ ህጎችን ጠንቅቆ በማወቅ ሲፈለግ የሚጠቅመን/የሚጎዳንን . . . ማለታችን ነው። ከፈጣሪ ቀጥሎ በዛች ተቋም እስካለን ድረስ እኛን በሚመለከት ለበጎም ለመጥፎም ይሁንታውን የሚሰጠውን ፍጡር ነው አለቃ የምንለው። ይህ ሰው በተለይ በቢሮክራሲው ውስጥ ደግሞ ሲፈልገው ጉዳያችንን የሚጎትት ሲያሻው ደግሞ በብርሀን ፍጥነት የሚፈጽምልን ነው። በመሆኑም እርምጃችን በአብዛኛው እሱ ባስቀመጠልን ፍጥነት የሚወሰን በመሆኑ አውቀንም ሆነ ሳናውቅ ሁለመናችን ላይ ተፅዕኖ ያለው ነው ማለት ነው። በአለቆች ሠፈር በአብዛኛው ሠራተኞች በፍላጎታቸው የሚፈጽሙ ሳይሆን እንጀራቸው ላይ የታሰረችው ልጓም ጎንበስ ቀና የምታደርጋቸው ሠዎች ናቸው። እናስ ማነው በልጓም ተይዞ እየተሳበ ዕድሜውን መግፋት የሚፈልገው? ለዚያ ነው አብዛኞቻችን አለቃ እንዲኖረን የማንፈልገው።

ከእልቅና በትይዩ የሚቀመጠው ደግሞ ከቅርብ አስርት አመታት ወዲህ ብዙ አውሮፓውያንና አሜሪካውያን እየፃፉበት የሚገኘው አመራር/መሪነት ነው። በነዚሁ ፀኃፍት ተደጋግሞ እንደሚወሳው መሪነት በሌሎች ላይ ውስጣዊ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ተፅዕኖ በመፍጠር የታቀደው ግብ ይሳካ ዘንድ ፈቅደውና ወደው የሚፈጽሙ ተከታዮችን ማፍራት መቻል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ፀሃፊዎቹ እንዳሉበት አለም ክህሎትና ዕውቀት የዳበረበት ማህበረሰብንና መሪን የሚጠይቅ ነው። በዚህ ሚዛን እኛ መሪዎችና ተመሪዎች በሚባለው ልክ ሆነን ባንገኝ የሚፈረደብን አይሆንም። ቶሎ ተምረን መቀየር አለመቻል ግን ይቅር የሚያስብል ስለማይሆን መትጋትን ይጠይቀናል።

አንድ ተቋም ወስደን መሪያችሁ ማነው ሲባል ከላይ “ለአለቃ” ከተሰጠው የተለየ ትርጓሜ የሚሰጥ ተከታይ ያለበት ድርጅት ማግኘት ብዙ ነው የሚል ግምት የለኝም። ምክንያቱም መሪዎቹ ከማህበረሰቡ እንደመውጣታቸው መጠን ያለንበት ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታው መሪዎች ተፈንጥረው እንዲወጡ በሚያስችል ሁኔታ ላይ እንዲገኙ አያደርግምና ነው። መሪያችሁ ማነው ሲባል በዘልማድ በድርጅታችን የስልጣን ዕርከን ቁንጮ ላይ የተቀመጠውን መጠቆም ቢኖርም ይህ ምላሽ የመሪነት ባህሪያትን በመገንዘብና በማወቅ የተመሰረተ ይሆናል ማለት አይቻልም። ሲጀመር በበዙ ተቋማት መሪ ሲባል አንድ የበላይ ኃላፊ ብተጠቀምም እርግጥ በተቋሙ ውስጥ ያለችው መሪ እሷና እሷ ብቻ ናትን ብለን ደግመን ስንጠይቅ በደበዘዘ ሁኔታ ብቅ ብለው እየደመቁ የሚሄዱ ሰዎችን ማየት የማይቀር ነው። ይህ ደግሞ ሲተነተን አለቆችም ሆኑ መሪዎች በየደረጃው እስከታችኛው ዕርከን ድረስ ይገኛሉ ማለት ነው። የተልዕኮ አፈፃፀም እንደመሪዎ ወይም አለቃዎ ባህሪና ችሎታ፣ እንደተከታዮቹ ሁኔታ፣ እንደአካባቢያዊ ሁኔታዎችና እንደመሪ-ተመሪ ወይም አለቃ-ምንዝር የግንኙነት መስተጋብር የሚወሰን ነው። ባለንበት የሥራ ዘርፍ በምናስማራቸው ሠራተኞች የሚኖረን ተቀባይነት በተጠቀሱት አራት ምክንያቶች ጥምረት እንደመሆኑ መጠን በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ሆነን አንዱ ሽፍት መሪ ከሌላው በበለጠ ተቀባይነት የሚያገኘው፣ አንዷ አስተባባሪ ከሌላው በበለጠ ተርብ የሆኑ ተከታዮችን የምታፈራው፣ አንዱ ቡድን መሪ ከእቻው በተለየ ዳተኛና የሥራ ፍቅር የሌላቸው ሠራተኞች የሚገጥሙት፣ አንዱ ኮሌጅ ከሌላው ኮሌጅ በተለየ በፍቅር የሚተያዩ የሥራ ቡድኖች የሚኖሩት . . . በዚሁ ልዩነት ምክንያት መሆኑን ልብ ማለት ይገባል።

> **እነዚህ ሠዎች … በተግባራቸው ሂደት ውስጥ የፍትህ መስፈን የሚያስጨንቃቸው፣ በራስ መተማመን የሚታይባቸው፣ ውሳኔ ለመስጠት የሚደፍሩ በተጠያቂነት ጊዜ ደግሞ ከሠራተኞቻቸው ፊት ሆነው ኃላፊነት የሚወስዱ እንዲሆኑ ይጠበቃል**

የመሪነት ሀ ሁ የሚጀምረው ከዕልቅና በመሆኑ በዚህ ላይ መገኘታችን ቅቡል ነው። አሳሳቢ የሚሆነው ሁሌም እዛው ላይ ተኝተን መገኘታችን ስለሚሆን መሻሻልን አልመን መጓዝ የግድ ነው። አሊያ መሪነት ተሰጧችን ነውን? ብሎ በመጠየቅ . . .።

የሰለጠነና ፈጣን የግንኙነት መረብ ተፅዕኖ ሰፊ በሆነበት በአሁኑ ዘመን መሪ መሆን ተሰጥኦና የዳበረ የአገልጋይነት አመለካከት ይጠይቃል። ሰውንና ተቋምን በህገ ልቡና፣ በጠቅላላ ዕውቀትና በፍጹም ቅንነት ብቻ መምራት የሚቻል ተግባር አይደለም። ይህም በመሆኑ ክብደቱን የተገነዘቡ ብልሆችና ቅኖች ስልጣንና ኃላፊነትን አድብተው የሚፈልጉ ሳይሆኑ ድንገት ሲመጣባቸው ለመቀበል ተጨንቀውና ተጠበው የሚወስኑ ናቸው። ኃላፊነት ሳይታሰብ፣ በግድ፣ በፍላጎት ወይም ድንገት በጫንቃችን ላይ ሊያርፍ ይችላል። መሪዎቻችን በየትኛውም መንገድ በመሪ ወንበር ላይ ሲቀመጡ ከተራው ዜጋ የሠፋና የጠለቀ ዕውቀትና አስተሳሰብ በተለይ በሚመሩት ዘርፍ ላይ እንዲኖራቸው ይጠበቃል። እናም መሪዎች የሚያሻቸውን ለይተው መማር፣ መተግበርና ከተመክሮ ዳግም ፈጥኖ በመማር ራሳቸውን መገንባት ይጠበቅባቸዋል። የመንግስትና የግል የውጭና የውስጥ የራስና የተቋም ጉዳዮች ልዩነትና ተዛምዶንም መለየት ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ ሠዎች ከተራ ተቋም ሠራተኞች የሚለዩት ሰውንና አስተሳሰብን ወደ አንድ በማምጣት ያልነበረ ውጤት የሚያመጡ በመሆናቸው ነው። በተግባራቸው ሂደት ውስጥ የፍትህ መስፈን የሚያስጨንቃቸው፣ በራስ መተማመን የሚታይባቸው፣ ውሳኔ ለመስጠት የሚደፍሩ በተጠያቂነት ጊዜ ደግሞ ከሠራተኞቻቸው ፊት ሆነው ኃላፊነት የሚወስዱ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ይህ ደግሞ በተለይ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ሲታይ መሪዎች በአግባቡ ዕውቀና የማያገኙና በቀላሉ የማይሸለሙ እንዲያውም ደፍረው በሰሯቸው ሥራዎች ተጠያቂነት ሲያደላ በሚችልባቸው ከባቢያዊ ሁኔታዎች የታጠሩ ከመሆናቸው አንፃር በዚህ ዘርፍ ላይ ኃላፊነት ሲወስዱ የአስተሳሰብ ማዕቀፋቸውን ማስተካከል ይጠይቃቸዋል። ከዚህ በመነሳት ማንም በየትኛውም ደረጃ ላይ መሪ ነን የሚሉ ሠዎች የሚከተሉት ቢያጤኗቸው ለሥራቸው በእጅጉ የሚያግዟቸው ይሆናሉ።

አንድ፡ በኃላፊነት የሚመራውን ዘርፍ በጥልቀት ለመረዳትና ለማወቅ ጉጉትና ፍላጎት የሌለው ሠው መሪ መሆን የለበትም። ከልምዳችን፣ ዕውቀታችንና ክህሎታችን በተለየ መስመር ሥራ እንድናስተባብር እና እንድንመራ የግድ የሚሉ አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ሁለት አማራጮች ይኖሩናል። አንድም ዘርፉን ለማወቅ መዘጋጀት አሊያም ይህን ኃላፊነት መሸከም እንደማንችል ተረድተን የሚችል ሰው እንዲይዘው ጥረት ማድረግ። አዲስ የምንገባበትን አካባቢ ለማወቅ ጉጉት እስካላሳደርን ድረስ ጥሩ መሪ በመሆን ውጤት ማስገኘት አንችልም። ሃኪም፣ የፋይናንስ ባለሙያ፣ ቴክኒሺያን የነበርን ሠዎች ከነበርንበት ወጥተን ጥሩ መሪ ወይም አስተማሪ ሊወጣን ይችላል - ጥልቅ የማወቅና የመማር ፍላጎት ከጨመርንበት። መርሳት የሌለብን በዚች አለም ላይ ማናቸውም ነገር ከሌላኛው ነገር ጋር ሁሌም በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የሚገናኝ መሆኑን ነው።

ሁለት፡ ሌሎች ያሰቡትንና እንዲያ እንዲያስቡ ያደረጋቸውን ጉዳይ ለመረዳት ሃሳብ - ቀና ሆኖ መገኘት ወሳኝ የመሪነት አመለካከት እምብርት ነው። ሌሎች ስለኔ የሚሉት ሊያቃኑኝ፣ ሊደግፉኝ፣ ሊያግዙኝና ሸክሜን ሊጋሩ ነው የሚል አስተሳሰብ በራስ ውስጥ መገንባት የመሪዎች የአስተሳሰብ አድማስ ስፋት

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከነሃሴ ወር ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ
Fetahi1717@gmail.com

ባለፈው እትም ተስፋሁን በተጠረጠረበት ወንጀል በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሆኖ ጉዳዩ ሲጣራ ቆይቶ ከወንጀሉ ነፃ ሆኖ ከተፈታ ዋል አደር ብሏል። በዚህ ሂደት ከወላጅ እናቱ ደብዳቤ ስለደረሰው በጣም ደስ ብሎታል። በሌላ በኩል ደግሞ የደብዳቤው መልዕክት በተለይ አይዞህ የሚለው ቃል አሁንም አሁንም በጆሮው ውስጥ እያንኳኳ ብቻውን እያወራ እያለ ከሄርሜላ ጓደኞች አንዷን በማግኘቱ እንደገና ተመልሶ ልቡ ሲሸፍት ስለተሰማው እንደገና ሊያገኛት ስለፈለገ ባገኜው አጋጣሚ እንዴት እንደሚያገኛት እያጣራ እንደነበር አንበብናል። ቀጣዩን ደግሞ አብረን እንከታተለው ………………….

ከእስር ቤት ከተፈታሁ በኋላ የእናቴን ደብዳቤ በማግኜቴ ከፍተኛ የሆነ ደስታ ቢሰማኝም ስለ እኔ የተጻፈውን መልዕክት ደግሞ ትልቅ የማንቂያ ደወል ስለሆነ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በጥሞና ለመከታተል አዕምሮዬን ለማሳመን ጥረት እያደረግሁ እያለ ባልጠበቅሁት ሁኔታ የሄርሜላን ጓደኛ ሳገኛት ደግሞ ያሰባሰብሁት ቆራጥነት እንደገና ሊናድብኝ ስላሰበ እሷን እያወራሁ ከአድማስ ባሻገር ስለ ሄርሜላ ማሰብ ጀመርሁ።

ይህ በዚህ እንዳለ ትንሽ አሰብሁና ሔርሜላን እንደምፈልጋት ትነግሪልኛለሽ በማለት ስፈራ ስቸር ነገርኳት፣ ምንም ችግር የለም ከክላስ እንደወጣች እነግራታለሁ አለችና ለሁሉም ችግር የለም እንደውልልሃለን አለች። እኔም በስልክ እንደማንገናኝ ሳውቅ ለጊዜው ስልክ ስላልያዝሁ መገናኜት ያለብን በአካል ነው። ስለዚህ ዛሬ ሰባት ሰዓት ላይ ከተማሪዎች መዝናኛ ክበብ እንዳገኛት ንገሪልኝ። አሁን የትምህርት ሰዓት እየደረሰብኝ ስለሆነ እቸኩላለሁ። አልኩና ተሰናብቻት ሄድኩ። እሷን ተለይቼ እየተጓዝኩ እያለ ከምኝታ ቤት ጓደኞቼ አንደኛው ጎጂ በማለት ሲጣራ ዘወር ስል እሷ እንደቆመች ወደ እኔ ስትመለከት ዐይን ለዐይን ስንገጣጠም እንደማፈር ብዬ በሩቁ እየተመለከትሁ ጓደኛዬን መጠበቅ ጀመርሁ። ከዚያም የሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ሰዓት በመድረሱ ክፍል ገባሁና እንደነገሩ ስከታተል ቆየሁ። ክፍለ ጊዜው ሲያልቅ ወደ ምኝታ ቤቴ በመሄድ አረፍ ብዬ ከጓደኛዬ የተላከልኝን ደብዳቤ በመክፈት አነበብሁት፣ ስለ ሐዋሣ ከተማ ውበት፣ ስለትምህርቱ እና ስለ አገር ቤት ቆይታችን ሃተታ ከፃፈ በኋላ በፍቅር ምክንያት ሳልዘናጋ ትምህርቴን መማር እንዳለብኝ የጻፈውን ሳነብ፣ በልቤ ያልተነካ ግልግል ያውቃል። በማለት ደብዳቤውን አጣጥፌ በኪሴ አስገባሁና ትንሽ ሣስብ ቆይቼ የእናቴን ደብዳቤ እንደገና ማንበብ ያዝሁ፣ እናቴ ለትምህርት ያላትን ፍላጎት እውን ለማድረግ ቆርጣ መነሳቷን እየደጋገምሁ አብሰለሰል ጀመር። ሳላስበው ከአልጋዬ ላይ እንደተኛሁ ደብዳቤውን የያዝሁበትን እጀን ወደ ታች በመዘርጋት ስሜት ውስጥ በመግባት ጣራ፣ ጣራውን ስመለከት የደብዳቤውን ይዘት ልቅም አድርጎ ያነበበው ጓደኛዬ ራቅ ብሎ ሁኔታዬን እተመለከተ ምነው ጎጂ ይህች ሦስት ሺ ብር ለምን፣ ለምን ተግባር እንደምታውላት ካሁኑ አስጨነቀችህ እንዴ! ችግር የለም ተመካክረን እንዴት እንደምታጠፋት ዘዴ አናጣም በማለተ ሲናገር አብረው ያሉት ሁሉ አልገባንም ይብራራልን ይሉት ጀመር። እኔም ቆጣ ብዬ ተው እንጅ የሰው ሚስጥርማ አታባክን አልሁና ደብዳቤዬን አጣጥፌ በመያዝ በንዴት ከአልጋዬ ላይ ፈጠን ብዬ ስወርድ እየሣቀ ወጥቶ ሄደ።

ከዚያም ትንሽ ቆየሁና ልክ ስድስት ሰዓት ሲሆን ወደ ምግብ ቤት አዳራሽ በመሄድ ምሣዬን በላሁና ሰባት ሰዓት ላይ ከተማሪዎች መዝናኛ ክበብ ሔርሜላን ስለቀጠርሁ ወደዚያው በማምራት እንዳለሁ ሣጅን ከኋላዬ ሆኖ ጠራኝና ዘወር ስል ሻሼ ደውላ ሲመችህ ደውልልኝ ብላለች አለኝ። እኔም ቶሎ ብዬ አመሰግናለሁ። አልሁና ከእሱ ጋር ላለመሄድ በመወሰን ወደ ፖስታ ቤት መሄድ እፈልጋለሁ አልሁትና ተለያዬን። ወዲያው ትንሽ ራቅ እንዳለ ዘወር ብዬ ወደ መዝናኛ ክበቡ ሄጄ በመቀመጥ ፊት፣ ለፊት ስመለከት ከሩቅ ሦስት ሆነው መጡ። ጉዟቸውን ቀጥለው ከኦዲተሪዬሙ አካባቢ ሲደርሱ ቆመው ሲያወሩ ቆይተው፣ ሌሎች ሲመለሱ ሔርሜላ ብቻዋን ነጠል ብላ ወደ መዝናኛ ክበቡ መምጣት ስትጀምር፤ የደስታ አይሉት የፍርሃት በውል ለይቼ የማላውቀው ጭንቀት የሠራ አካላቴን ወረረው። እየቀረበች ስትመጣ እንደምንም ያለ የሌለ የድፍረት ወኔዬን አሰባስቤ ከተቀመጥሁበት በመነሣት ለሰላምታ ስዘጋጅ ሃይ! ተስፍሽ በማለት እጇን ዘርግታ ተቃቅፈን ሰላምታ ተለዋወጥን። ከዚያም እየተቀመጥን እያለ ምነው? ጠፋህ! ለነገሩ ሰሞኑን ችግር ላይ እንደነበርህ ሰምቻለሁ። እንዴት ነው? በሰላም ለቀቁህ ስትለኝ የምለው እየጠፋብኝ በድንንጋጤ አይ! ሰላም ነው። አንችስ ደህና ነሽ በማለት ዐይን ዐይኗን ስመለከታት በጣም ደህና ነኝ አለችና እሽ! አሁን ምን መውሰድ ትፈልጋለህ አለችና ከሄድሁበት የኃሳብ ጎዳና አስመለሰችኝ። እኔም ጋባዡማ እኔ ነኝ እስከምትረጋጊ ብዬ ነው እንጅ አልሆና ፍላጎቷን ስጠይቃት ችግር የለም ሌላ ጊዜ ደግሞ አንተ ትጋብዘኛለህ ስትለኝ ቶሎ ብዬ ይልቅ ምን እንደምትፈልጊ ንገሪኝ አልሁና ስነሣ በቃ ስፕራይትና ዶናት አለችኝ። ወዲያው ለእሷም ለእኔም የሚሆነውን ክፍያ በመፈፀም ይዤ መጣሁና ከለስላሣው ጋር ዶናቱን አብረን መብላት ቀጠልን። ይህም ሆኖ አሁንም ፍርሃቴ እንዳለ ነው። ብቻ ደግነቱ ምን ብዬ አወራታለሁ እያልሁ ስቸገር እሷው የተለያየ ርዕስ እያነሣች ኃሳብ ለኃሳብ መለዋወጥ ስለጀመርን ቀስ በቀስ እየተረጋጋሁ ሄድሁ። እናም ቆየት ብላ ለምን እንደታሠርሁ ስትጠይቀኝ። እኔም መልሼ እንዴት እንዳወቀች ስጠይቃት፤ ‹‹በቃ አወቅን ከእኛ የሚሰወር ነገር የለም። እኛ እኮ የመረጃ መረባችን ቀላል አይደለም። ደግሞ እኮ ብዙ ሰዎች ስለአንተ ደህንንነት የሚጨነቁና በሪሞት ኮንትሮል የሚከታተሉህ ስላሉ መረጃው በቀላሉ ይደርሰን ነበር።›› በማለት ሣቋን ለቀቀችው። አቤት የድምፅዋ ለዛና አሣሣቋ ሲያምር እንደገና በመላ ሰውነቴ ዘልቆ ሲገባ ይሰማኝ ጀመር። ከዚያም አከታተለችና ‹‹አባቴ ይሙት ልንጠይቅህ አስበን ነበር። ብቻ የታሰርህበትን ቦታ በደንብ ስላላወቅን ይቅርታ እንደምታደርግልን እርግጠኛ ነኝ።›› አለችና እሷም በፊንታዋ አተኩራ ትመለከተኝ ጀመር። መቼም ዐይኗ እና ጥርሷ ለጉድ ነው። ቀና ብላ ስትመለከተኝ የዐይኗ ጨረር የሆነ ምትሃት ያለው ይመስል ኤሌክትሪክ እንደነካው ሰው ሰውነቴን ነዘረው። እኔም እንደምንም ተደፋፈርሁና ለመሆኑ ስለ እኔ የሚያስቡ ብዙ ሰዎች ያልሻቸው እነማን ናቸው? በማለት ስጠይቃት፤ ‹‹በእውነቱ በጣም የሚያስቡና የሚጨነቁ አሉ። እንዲያውም ከእስር ቤት የወጣኸው በእነሱ ፆምና ፀሎት ሣይሆን አይቀርም።›› አለችና ዳግም ሣቀች። እኔም አባባሏ ስላስገረመኝ አብሬ ሣቅሁ። ከዚያም በመካከላችን ለተወሰኑ ሴከንዶች ፀጥታ ሰፍኖ እንደቆዬ ጉሮሮዬን በመሞረድ አንችን ለማግኜት ያልሞከርሁት ያልወጣሁት ዳገት አልነበረም። ባለፈው ብሉ-በርድ ካፌ ቀጥረሽኝ ካሁን፣ አሁን ትመጫለሽ እያልሁ ስጠብቅ ያልጠበቅሁት ችግር ደርሶብኝ ነበር። በማለት በጊዜው የተከሰተብኝን ሁኔታ በዝርዝር ስነግራት በአንክሮ ስትመለከተኝ ቆይታ ስጨርስ ‹‹ወይኔ ምስኪን!›› አለችና ራሷን በማወዛወዝ ሃዘኔታዋን ከገለፀች በኋላ፤ ‹‹እኔ እኮ በጊዜው ስደውል ስልክህን የያዘችው እህትህ ስለነበረች መልዕክት አስተላልፌ ነበር። በእርግጥ ችግሩ ከቁጥጥሬ ውጭ ስለሆነ እንጅ፣ ሆን ብዬ አልነበረም። ነገር ግን ለሌላው ጊዜ አጣሁሽ ለምትለው ስታካብድ ነው እንጅ ያን ያህል አንተ ፈልገኸኝ ስለጠፋሁ አይመስለኝም›› በማለት ፈገግ አለች።›› እኔም መልሼ ነገሮችን ለመሸፋፈን ያህል ያው ያኔ መታወቂያዬን አግኝተሽ በመስጠት ከብዙ ችግር ስላወጣሽኝ እንዴት ሻይ ቡና አልላትም በሚል ነበር ስላት፣ ያን ጠገራ ብር የሚመስለውን ዐይኗን እያቁለጨለጨች ከአንገቷ ዝቅ በማለት አመሰግናለሁ! አለችኝ። ይህ በዚህ እንዳለ ሰዓቷን ተመለከተችና በል እንግዲህ ይቅርታ ክላስ ስላለኝ፣ ከዚህ በላይ መቆየት አልችልም። አለችና ከመቀመጫዋ ተነሣች። ከዚያም ልሸኝሽ በማለት አብረን ግራና ቀኝ ሆነን እየተጓዝን እያለን ‹‹በጣም የሚገርመኝ አንድም ቀን ወደ ምግብ ቤት ስትሄጅ አይቼሽ አለማወቁ ነው።›› በማለት ስናገር፤ ከት ብላ ሳቀችና ‹‹እኔ እኮ ነን ካፌ ስለሆንሁ እዚህ አልበላም›› ስትለኝ ወዲያውኑ ምንም እንኳን አዕምሮዬ ባይቀበለውም በመካከላችን ልዩነት እንዳለ ሣውቅ፣ ለአንዴ የሆነ ነግር እንደ በረዶ ሲቀዘቅዘኝ ተሰማኝ።›› ወዲያው በዚያን ጊዜ ሳደርገው የነበረው በምግብ ቤት አካባቢ እሷን ለማግኘት የነበረው የፍለጋ ሥራ ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደነበር ስገነዘብ ሣላስበው ሣቄን ለቀቅሁት። እሷ ቀና ብላ እየተመለከተችኝ ምነው? የእኔ ነን ካፌ መሆን ያስቃል እንዴ አለችና እሷም አብራ ስትስቅ፣ መሣሣቴን አወቅሁና አይ በዚህ ሳይሆን የሆነ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው። በማለት ከነገርኋት በኋላ፣ ዝም ብለን ትንሽ እንደተጓዝን….. ወደ እኔ እየተመለከተች በቅርቡ…. ለብርቱ ጉዳይ ስለምፈልግህ እንደምንም አቻችለህ ቀጠሮ ትይዝልኛለህ። አለችና ልቤን አንጠለጠለችው። እኔም በልቤ ደስ እያለኝ ችግር የለም በማለት ምላሽ ሰጠሁ። ከዚያም ወደ መማሪያ ክፍላቸው እንደደረስን በዚያ አለንጋ ጣቷ እጀን በመጨባጥ ተሰናብታኝ ስትሄድ በዓይኔ ሸኜኋት።

**ይቀጥላል!**

# Freshman Memories ...

continued from page 4

therefore, they begin to realize that each incident has something different to nourish or embrace their lives into this dynamic world.

In some cases, it is no sooner than they settle themselves that they begin to understand that things are not as scary as they thought they would be, and they even may start imagining campus life as their home. They can further start imagining how they would pass the next four years of their academic life recognizing themselves well and assuming what they want to do. While they are here, it will be absolutely clear that they have to accept the unknown and adapt the new environment surprisingly far from their comfort zone as a university student. In fact, this is what makes campus life unique.

In our life, we have taken many journeys without which we would not have explored important truths. Indeed, these are the facts and realities that will add texture and meaning to our life. On the other hand, the broad spectrums of life experiences are only illuminated if they are colored by students' ambition and commitment in a college as this is turning point that determines the future prospects of their lives. That is why they gradually start to realize that they have to go through life challenging and being challenged.

Days elapse and months move very fast to count years during which; however, students' nestle their life gleaned from experiencing many cultures. Can you imagine the incredible changes they all undergo in a short a time? Have you ever imagined the new relationships formed and their own personal transformation into one to the other? Amazing as it is, the long transition from freshman year to senior is finally over. Anyways, for when all these things have been lost, only memory remains in their worldly life forever as students' mind is like a sponge which absorbs every part of their life.

# መረጃና የመረጃ ምንጮች ቁማር

ጀማል ሙሀመድ ሀይሌ (ዶ/ር)
ከጋዜጠኝነትና ስነተግባቦት ትምህርት ክፍል
jemalmohammed99@gmail.com

በደርግ ዘመን አንዲት ለዘመናዊ እርባት የተፈለገች የፈረንጅ ላም ወደ ኢትዮጵያ እንድትመጣ ከተደረገ በኋላ እርባታዋ ፓዊ ውስጥ እንዲካሄድ በተወሰነው መሰረት ወደ እዚያው ትላካለች፡፡ ከተወሰነ አመት በኋላ ስለእርባታዋ ሁኔታ መረጃ ወይም ሪፖርት እንዲቀርብለት ይጠይቃል - አዲስ አበባ የሚገኘው የግብርና ሚኒስቴር፡፡

ከእርባታው ቦታ ያሉት ባለሙያዎች አንድ ጥጃ መውለዷን ለወረዳው ግብርና ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም የወረዳው ግብርና “አንድ ጥጃ ወልዳለች” ብሎ ለአውራጃው ግብርና ሪፖርት ማድረግ ደበረው፤ “አንድ” የሚለው ቁጥር አነሰበት፡፡ ስለሆነም “ሁለት ጥጃ ወልዳለች” በማለት ለአውራጃው ግብርና ሪፖርት አደረገ፡፡ የአውራጃው ግብርና በበኩሉ ሁለት የሚባል ቁጥር አልጣመውም፡፡ እስካሁን ገና ሁለት ብቻ ከወለደችማ አብዮታዊ ቁርጠኝነት በአውራጃው ውስጥ የለም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም “ሶስት ጥጃ ወልዳለች” በማለት ለክፍለ ሀገሩ ግብርና መምሪያ ሪፖርት አደረገ፡፡ የክፍለ ሀገሩ ግብርና በበኩሉ “ሶስት ጥጃ ወልዳለች” በማለት ሪፖርት ማድረግ ክፍለ ሀገሩን የሚያስገምት/የሚያስገመግም ሆኖ አገኘው፡፡ ቢያንስ አንድ ቢጨምርበት ይሻላል፡፡ ስለሆነም “አራት ጥጃ ወልዳለች” በማለት ለግብርና ሚኒስቴር ሪፖርት አደረገ፡፡ እናም የአንድ የፈረንጅ ጥጃ ውልደት ሪፖርት አዲስ አበባ ሲደርስ አራት ሆኖ አረፈው ይባላል፡፡

ሁሉም እውቀት የሚጀምረው በመረጃ ነው፡፡ ያለ መረጃ እውቀት የለም፡፡ መረጃ የሌለው ሰው ወይም ህዝብ እውቀት የለውም፡፡ እውቀት የሚገኘው ከመረጃ ነውና እውቀት የመረጃ ጥገኛ ነው፡፡ እውቀት ይቅርና ድንቁርናና ማይምነትም ቢሆኑ የሚታወቁት በመረጃ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አለማወቅን ለማወቅ መረጃ ያስፈልጋል፡፡

መረጃ የእውቀት ብቻ ሳይሆን የሀብትም ምንጭ ነው፡፡ ድሆች የገንዘብ ብቻ ሳይሆን የመረጃም ድሀ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለፅ መረጃ ስለሌላቸው እውቀት የላቸውም፤ እውቀት ስለሌላቸው ሀብት የላቸውም፡፡ ሀብታሞች የገንዘብና የንብረት ብቻ ሳይሆን የመረጃም ሀብታም ናቸው፡፡ ያለ መረጃ ሀብት ሊገኝ ወይም ሊመጣ አይችልም - ሀብቱ ወይም ንብረቱ በውርስ/በሎተሪ የተገኘ ካልሆነ በስተቀር፡፡ በውርስ የተገኘ ሀብትም በመረጃ ሀብት ካልተደገፈ ማለትም በመረጃና ከመረጃ በሚገኘው እውቀት ላይ ተመስርቶ ጥቅም ላይ ካልዋለ እድሜ አይኖረውም፡፡

በሙስና ወይም በማጭበርበር ከሚገኝ ሀብትና ንብረት በፊት ያለው ነገርም መረጃ ነው፡፡ እንዲያውም በሙስና ለሚገኝ ሀብትም ሆነ ንብረት መረጃን መያዝና መጠቀም ብቻ በራሱ በቂ አይደለም፡፡ በሙስናና በማጭበርበር የሚገኝ ሀብት መረጃን ከመረጃነቱ በላይ መጠቀምን ይጠይቃል፤ ማለትም መረጃውን በተምታታ መንገድ ስራ ላይ ማዋልን (manipulate ማድረግን) ግድ ይላል፡፡ በሌላ አነጋገር ጥቅሙ የሚገኘው መረጃ በመያዝ ወይም በማግኘት ከሚገኘው እውቀት ሳይሆን በመረጃው ላይ በመቆመር ነው፡፡ የሚገኘው “ጥቅም” መጠንም ሆነ ቀጣይነት ግለሰቦቹ ባላቸው በመረጃ ላይ የመቆመር ብቃት ወይም “ጥበብ” ይወሰናል፡፡ ማን ነበር “ከያንዳንዱ ትልቅ ሀብት ጀርባ ትልቅ ወንጀል አለ” ያለው? እኔ ደግሞ ይህን ወርቃማ አባባል አንድ ርምጃ ወደ ፊት ልውሰደው፤ ለትልቅ ሀብት ከሚያበቃ ከያንዳንዱ ትልቅ ወንጀል ጀርባ፣ በመረጃ ላይ የሚከወን ትልቅ ቁማር አለ፡፡

አንዳንድ የግንባታ ተቋራጮች በአንድ አካባቢ ወይም ከተማ የሚወጡ የግንባታ ጨረታዎችን ለመቆጣጠር ስለሚጠቀሙበት ስልት ከጥቂት አመታት በፊት የሰማሁት ወሬ እዚህ ላይ ትንሽዬ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡ (ስልቱ አሁን በስራ ላይ ይኑር የማውቀው ነገር የለም፡፡) አንድ የግንባታ ጨረታ ማስታወቂያ ሲወጣ ተመሳሳይ የግንባታ ደረጃ ያላቸው ተቋራጮች ማስታወቂያውን ላወጣው መ/ቤት ወይም ተቋም የታሸገ የጨረታ ሰነዳቸውን ወቅቱን ጠብቀው ያስገባሉ፡፡ የጨረታ ሰነዳቸውን እያሸጉ ያስገቡና በየፖስታው የታሸጉት ሰነዶች ገና ያልተከፈቱ ቢሆንም ማን እንደሚያሸንፍ ግን ለእነሱ ሚስጥር አይደለም፡፡ ሚስጥርነቱ “ለየዋሁ” መ/ቤት ወይም ተቋም ብቻ ነው፡፡ ለምን? ተቋራጮቹ ሰነዱን ያዘጋጁት አንድ ላይ ሆነው ወይም ተነጋግረው ነው፡፡ ስለዚህም የአንዱን ዋጋ ሌላው ያውቀዋል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ በዚህ ጨረታ ማን ማሸነፍ እንዳለበት ወስነው ነው የዋጋ ተመናቸውን ያስቀመጡት፡፡ ሌሎቹ ተቋራጮች፣ በጨረታው እንዲያሸንፍ ተረኛ የሆነው ተቋራጭ ካቀረበው ዋጋ በላይ ከፍ አድርገው ያስገባሉ፡፡ ይህ ስልት ወይም የመረጃ ላይ ቁማር በተቋራጮች “ማፈን” ተብሎ እንደሚታወቅ መስማቴም ትዝ ይለኛል፡፡ “የየዋሁ” መ/ቤት ወይም ተቋም አመል ደግሞ ይታወቃል - አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን መምረጥ፡፡

> መረጃ የእውቀት ብቻ ሳይሆን የሀብትም ምንጭ ነው፡፡ ድሆች የገንዘብ ብቻ ሳይሆን የመረጃም ድሀ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለፅ መረጃ ስለሌላቸው እውቀት የላቸውም፤ እውቀት ስለሌላቸው ሀብት የላቸውም፡፡

“ማፈን” በመረጃ ላይ ለመቆመር ስራ ላይ እንደ ዋለ ግልፅ ነው፡፡ በመረጃ ላይ የተቆመረው ግን ውድድር ወይም ጨረታ እንዳይካሄድ በማድረግ የሚፈለገው ተቋራጭ እንዲያሸንፍ ለማድረግ ብቻ አይደለም፡፡ ዋጋውን ለማናርም አገልግሏል፡፡ እንደምን? በጨረታው “ተሸናፊ” የሚሆኑት ተቋራጮች ዋጋ የሚያስቀምጡት በጨረታው “ለማሸነፍ” ተረኛ የሆነው ተቋራጭ ዋጋ ካስቀመጠና የእሱን ዋጋ ካወቁ በኋላ ከእሱ ዋጋ በላይ እየጨመሩ ስለሆነ የሚያሰጋው ነገር የለምና ዋጋውን በጣም-በጣም እንዲያተርፈው አድርጎ ይሰራዋል፤ ወይም ይቆልለዋል፡፡ ዝቅተኛ ዋጋ አይቶ አሸናፊነትን በመስጠት አባዜ ለተለከፉት የጨረታ ኮሚቴ አባላት ወይም የመ/ቤት ሀላፊዎች ግን የዚህ ተቋራጭ ዋጋ ዝቅተኛ ብቻ ሳይሆን በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ሙሰኛ የሆነ የመ/ቤት ሀላፊ “ባለድርሻ አካል” ሆኖ ብቅ ካለም ሌላው የመረጃ ቁማር ገፅታ ይሆናል - የቁማሩን ቀመር ይበልጥ የሚያራቅቅ፡፡

ከዚህ የከፉና የለየላቸው የመረጃ ቁማርተኞችም አሉ፡፡ የእነዚህኞቹ ቁማር - አላማቸው ምንም-ይሁን-ምን - መረጃውን ራሱን መፍጠር ነው - “በሬ ወለደ” አይነት፡፡ የሀሰት መረጃዎችን ይፈበርካሉ፤ በትንሹ “ደራሲ በአሉ ግርማ በጣና ደሴቶች ውስጥ በምነና እየኖረ ነው” በማለት በፌስ ቡክ የተነዛውን አይነት ወሬ፤ በትልቁ “ሳዳም ሁሴን ጅምላ ጨራሽ መሳሪያ አለው” በማለት አሜሪካ ኢራቅን ወንጅላ የወረረችበትን አይነት “መረጃ”፡፡

መረጃ ሰጪዎች ወይም የመረጃ ምንጮች ሳያውቁት ከመረጃ ቁማር ላይ የሚወድቁበት ጊዜ ያለ ቢሆንም፣ አብዛኛውን ጊዜ ግን አውቀውት ነው የሚፈፅሙት፡፡ አሁን ባህር ዳር ከተማ የአማራ ክልል ስራ አመራር አካዳሚ ካለበት ቦታ ላይ ቆርቆሮ-በቆርቆሮ (ጣሪያም ቆርቆሮ፣ ግድግዳም ቆርቆሮ) በሆኑ ቤቶች ነበር የስራ አመራር ስልጠና በአማራ ክልል የተጀመረው፡፡ አንዳንዶች “ካምብሪጅ” ሌሎች ደግሞ “አምስት ኪሎ” በማለት ያሸሟጥጡበት እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ በ1990 አካባቢ በስልጠናው እንድሳተፍ ከቀድሞ መ/ቤቴ ተመድቤ ገብቼ ነበር፡፡ ከመረጃ ጋር የተያያዘ አንድ ገጠመኝ አለኝ፤ እሱን ላንሳ፡፡

አንድ ቀን ምሽት በአንድ ቡድን ውስጥ ያለነውና አንድ ክፍል ውስጥ የተመደብነው ሰልጣኞች እንደ ተለመደው በውይይት ላይ ነን፤ ወደ አስራ ስድት አካባቢ እንሆናለን፡፡ ለጉዳዩ መነሳት ሰበብ የሆነውን ዋናውን ርእሰ ጉዳይ ባላስታውሰውም የተወያየንበት ቅርንጫፉ ርእሰ ጉዳይ ግን በውል ይታወሰኛል፤ ከበታች የመንግስት መ/ቤቶች ወደ በላይ መ/ቤቶቻቸው ስለሚላክ ሪፖርት የተአማኒነት ጥያቄ ነበር፡፡

የመንግስት መ/ቤቶች የተቋቋሙት መንግስት ሊደርስበት የሚፈልገው ግብ ስላለ ያን ግብ ለማሳካት ነው፡፡ የታሰበውን ግብ ለማሳካት ደግሞ የተለያዩ ስራዎችን “አንድ፣ ሁለት…” በማለት ዘርዝረው ማቀድ አለባቸው - ወደ እዚያ፣ ወደ ታለመው ግብ የሚያደርሱ ተግባሮችን በመለየት፡፡ መፈፀም የማይቻል ወይም ለመፈፀም የሚያዳግት ነገር አይታቀድም፡፡ ከመንግስት በሚመደብ በጀት ወይም በእጅ በሚገኝ ሀብት (የሰው፣ የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ የጊዜ፣ ወዘተ.) ሊሰራ የሚችለው ተግባር ተለይቶ ነው የሚታቀደው፡፡ ይህም ሆኖ ታቀደ ማለት በርግጠኝነት ይከወናል ማለት አይደለም፤ በተለያዩ ምክንያቶች አፈፃፀሙ ሊጓደል ይችላል፡፡ አመች ሁኔታዎች በመሟላታቸው ሙሉ በሙሉ ወይም ከታሰበው በላይ ሊከወንም ይችላል፤ የእቅዱ 150 ወይም 200 “ፐርሰንት” አይነት አፈፃፀም ከሆነ ግን የአስተቃቀድ ችግሩን አጉልቶ ማሳየቱ አይቀርም፡፡

ያም ሆነ ይህ የታቀደ ተግባር መሰራት ያለበት የመሆኑን ያህል ሪፖርት መደረግም አለበት፡፡ እናም የበታች (ለምሳሌ የወረዳ፣ የዞን) መንግስት መ/ቤቶች ለበላይ (ለምሳሌ ለክልል) መ/ቤታቸው በየበጀት አመቱ እቅድ ማቅረባቸውና በየሩብ አመቱ ሪፖርት ማቅረባቸው የተለመደ አሰራር ነው፡፡ መነሳት ያለበት ጥያቄ እቅዱ ሳይሆን ሪፖርቱ ምን ያህል ታእማኒነት አለው? የሚለው ነው፡፡ በዚያ ጉዳይ ላይ የ“ካምብሪጁ” የአንድ ቀን ምሽት ውይይታችን ተጧጧፈ - አልፎ-አልፎም በልማዳዊው ጭቅጭቃችን እየታጀበ፡፡

ከወረዳና ከዞን የመጡ የተወሰኑ የቡድናችን አባላት ሪፖርት ወደ የበላይ መ/ቤት ሲላክ (ማለትም ወረዳው ወደ ዞኑ፣ ዞኑ ወደ ክልሉ ሲልክ) የተሰራውና

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# እንግዳችን

## "የመምህራን የምርምር ተሳትፎ የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ አለበት"

አቶ ባየህ አበራ

**የዚህ ወር እንግዳችን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ2007 ዓ.ም ምርጥ ተመራማሪዎች መካከል ግንባር ቀደም ናቸው። የምርምር ተሞክሯቸውን አስመልክቶ ከናይል ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል። ቃለ መጠይቁን እነሆ። መልካም ንባብ!**



ናይል፡- በመጀመሪያ ስምዎትንና የሥራ ኃላፊነትዎን ቢያስተዋውቁን?

አቶ ባየህ፡- ስሜ ባየህ አበራ በየነ ይባላል የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህር ስሆን በአሁኑ ሰዓት የኃላፊነት ቦታ የለብኝም።

ናይል፡- የትውልድ ቦታዎንና የአስተዳደግ ሁኔታዎን ቢገልፁልን?

አቶ ባየህ፡- ተወልጀ ያደኩት ከባሕር ዳር 80 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ዳንግላ ወረዳ የገጠር ቀበሌ ልዩ ስሙ «ጉምድሪ» በሚባል ቦታ ነው።

ናይል፡- ስለ ቤተሰብዎ ቢያጫውቱን?

አቶ ባየህ፡- ባለትዳርና የ3 ልጆች አባት ነኝ።

ናይል፡- በህይወትዎ የሚወዱት ነገር ምንድን ነው? የሚጠሉትስ?

አቶ ባየህ፡- የምወደው ተፈጥሮን ማድነቅ እጅግ በጣም የሚያስደስተኝ ሲሆን ሰዎችን በቻልኩት መጠን ሁሉ መርዳት ያስደስተኛል። በትርፍ ሰዓቴ ከጓደኞቼ ጋር መጫወት፣መዝናናት  የምጠላው ደግሞ ያለምንም ሥራ አእምሮንና ጉልበትን ማባዘን ነው።

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መቼ ሥራ ጀመሩ? ከዩኒቨርሲቲው ውጭ የሰሯቸውን ስራዎች ቢገልፁልን?

አቶ ባየህ፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሥራ የጀመርኩት በሚያዚያ ወር 2000 ዓ.ም ላይ ሲሆን የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅን ከመሰረቱት መካከል አንዱ ነኝ። ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሥራ ከመጀመሬ በፊት በአማራ ክልል ጤና ቢሮ ሥር ባሕር ዳር ጤና ምርምር ቤተ-መከራ ማዕከል ከሰኔ 1993 ዓ.ም እስከ መስከረም 1998 ዓ.ም ድረስ ለአምስት ዓመት ያህል ሰርቻለሁ። ከዚያ በመቀጠል ለ1 ዓመት ተኩል ያህል አልካን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኃላፊነት ቦታ (ዲን) ሆኘ ሰርቻለሁ።

ናይል፡- በ2007 ዓ.ም ባበረከቷቸው 15 የምርምር ውጤቶች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ምርጥ ተመራማሪ ሆነው በመመረጥዎ በናይል ጋዜጣ ስም እንኳን ደስ አለዎ እያልን ስለምርምሮቹዎ ትንሽ ቢያጫውቱን?

አቶ ባየህ፡- አመሰግናለሁ የግለሰቦች የጥረት ውጤት (ስኬት) የተቋም ስኬትና ጥረት ስለሆነ እናንተም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ አካል ስለሆናችሁ ማለትም የናይል ጋዜጣ አዘጋጆች ደስ እንደሚላችሁ እርግጠኛ ነኝ።

ከምርምር ውጤቶችና ህትመት ጋር ተያይዞ መግለፅ የምፈልገው እነዚህ 15 የምርምር ህትመቶች በእኔ ብቻ የተሰሩ አለመሆኑን ነው፤ ስለዚህ በዋና ተመራማሪነት እና በአጋርነት  የሰራኋቸው ናቸዉ። ከነገር ግን አንድም ምርምር ብቻየን የሰራሁት የለም። ስለዚህ ምርምሮች ከተለያዩ አካባቢዎች ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ተመሳሳይ ሙያ ካላቸው ባለሙያዎች በጋራ (Collaboration) የተሰሩ ናቸው። ምክንያቱም ጥራቱን የጠበቀና ችግርን መሰረት ያደረገ ምርምር በአንድ ተመራማሪ ብቻ የሚሰራ ከሆነ የሚያስገኘው የመፍትሄ ሀሳብ አመርቂ የመሆን እድሉ ዝቅተኛ ስለሚሆን ነዉ።

ናይል፡- የምርምር ውጤቶቹ በምን ጆርናል (መጽሄት) ላይ ነው የታተሙት?

አቶ ባየህ፡- ከተሰሩት 15 የምርምር ህትመቶች መካከል አስሩ የታተሙት በ "Science Citation index (SCI)" በሚገኙና በዓለም ዓቀፍ የሚታወቁ መጽሄቶች ነው። ለመጥቀስ ያህል "**PLOS ONE, BMC Pharmacology and Toxicology, Journal of Tropical Doctor, Journal of Water, Sanitation and Hygiene**" የመሳሰሉት ይገኙበታል። ሌሎች አምስቱ ደግሞ በታወቁና "Peer reviewed" ከሆኑ መፅሄቶች ሲሆን አስራ አምስቱም ህትመቶች በአሁኑ ሰዓት "Predatory Journal" (ደረጃቸውን ያልጠበቁ መጽሄቶች) ከሚባሉት አሳታሚ መጽሄቶች ውስጥ የሉበትም።

ናይል፡- የምርምር ውጤቶቹ የትኩረት አቅጣጫዎች በምን ዙሪያ ናቸው?

አቶ ባየህ፡- ጥሩ ችግር ፈች (Operational) ምርምር ማካሄድ ማለት በአጭሩ በችግሮች ላይ ሣይንሳዊ ዘዴ በመጠቀም በስልትና፣ በጥልቀት መፈተሽ፣ መረዳት እና የመፍትሄ ሀሳብ ማምጣት ነው። ስለዚህ ትኩረት ለይቶ ምርምር መስራት የግድ ነው። የራሴ ምርምር የትኩረት አቅጣጫ ከሁለት መሰረታዊ ነገሮች የተነሱ ናቸው፡-

1. ከራሴ የትምህርት ክህሎትና መስክ ጋር ሴሆን
2. ከሀገራችን የጤናና የምርምር የትኩረት አቅጣጫ (themes) ጋር የተያያዙ ናቸው። ስለዚህ በዋናነት የህብረተሰብ የጤና ችግር ከሆኑ ተላላፊ በሽታዎች ጋር በተያያዙ ችግሮች ላይ ሲሆን በአይን የማይታዩ ጥቃቅን ህዋሳት (Bacteria virus, fungi and parasites) ዙሪያ ነው። በአጭሩ ለመግለፅ፡-

- በሽታ አምጭ ተዋስያን መለየት እና ተዛማችነታቸዉን፣ ስርአታቸዉን እንዲሁም ባህሪያቸውን ማጥናት
- ከመድኃኒት ጋር ያላቸውን ተለማማጅነት ማጥናት
- ከውሃ፣ ከምግብ፣ ከግልና ከአካባቢ ንፅህና ጋር ከሚያያዙ በሽታዎች ላይ ነው።

ናይል፡- ምርምሮቹ ወደ ማህበረሰቡ ደርሰው ችግር እንዲፈቱ ምን ሥራ

⇨

# እንግዳችን …

እየሰሩ ነው?

አቶ ባየህ፡- የምርምሮች መነሻ የማህበረሰብ ችግሮች እስከሆኑ ድረስ የምርምር ውጤቶች በህትመት ታትመው በመደርደሪያ ላይ ተቀምጠው ለማህበረሰቡ ሳይደርሱ መቅረት የለባቸውም፡፡ ስለዚህ የተደረጉ ሙከራዎችን ልናገር፡-

1. የግርሻ በሽታን በተመለከተ ጥናቱ ባስቀመጠው መሰረት በሽታው በብዛት በሚከሰትባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በስፋት ት/ት ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ሥራ የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት እውቅና ሰጥቶናል በመረጃነትም ተይዟል፡፡ የማስተማሪያ «manual” ተዘጋጅቷል፡፡
2. ከ1ኛ ደረጃ ት/ት ቤቶች ውስጥ በ3 ት/ት ቤቶች ላይ የአንጀት ውስጥ ትላትልን በተመለከተ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ እነዚህ የተሰሩት ከባሕር ዳር ከተማ ጤና ጥበቃ ጽ/ት ቤት ጋር ነው፡፡
3. በራሴ በኩል ለማስተምረው ት/ት የምርምር ውጤቶችን ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ለማስተማሪያነት እጠቀምባቸዋለሁ፡፡
4. የምርምር ውጤቶች በተለያየ ጊዜ በሚካሄዱ የሀገር እና ዓለም አቀፍ ጉባዔ ላይ በተለያዩ ዘዴዎች ለማስተላለፍ ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ወደ ሚመለከተው ባለድርሻ ወይም ማህበረሰብ ደርሰዋል ማለት አይቻልም፡፡

ናይል፡- የምርምር ሥራዎችን ለመሥራትና በታዋቂ መጽሄቶች ላይ ለማሳተም ምን ያህል ጊዜ ወሰደ? ለማሳተም የነበረውን ውጣ ውረድ ቢያጫውቱን?

አቶ ባየህ፡- ይህ ጥያቄ በጣም ጥሩ ነው ምክንያቱም በአንዳንድ የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ ክፍሎች እንዴት በአንድ 1 ዓመት ውስጥ 10 ወይም 15 የጥናት ህትመቶች ይሰራሉ የሚሉ ብዥታዎች ስላሉ ነው፡፡ ይህ እኔም ተማሪ እያለሁ የማነሳው ነበር፤ የሁለተኛ ዲግሪዬን እንግሊዝ ሀገር በምሰራበት ወቅት የእኔ ፕሮፌሰር ከ250 በላይ ህትመቶችና 5 መጽሐፍቶች ነበሩት፤ እኔ እንዴት ይቻላል? የሚል ሀሳብ ነበረኝ፡፡ ስለዚህ ባጭሩ እነዚህ 15 ህትመቶች ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በመሰራት ላይ የነበሩና ሙሉ ህትመታቸው በ2007 ዓ.ም የታተሙ ናቸው፡፡

በታወቁ መጽሄቶች ለማሳተም ቢያንስ ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት የሚደርስ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ ለማሳተም ከገጠሙኝ ውጣ ውረዶች በዋናነት የምገልፃቸው፡-

- ✓ ክፍያ የሚጠይቁ ታማኝ የምዕራባዊን መፅሄቶች
- ✓ ምርምር የተሰራበት ቤተ ሙከራ በዓለም አቀፍ “Accredited” ነዉ ወይ የሚሉ አሳታሚዎች
- ✓ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችግሮች ይታይበታል የሚሉ ወዘተ.. በዚህ አጋጣሚ የቋንቋ ባለሙያዎችን እርዳታ የጠየኩበት ጊዜ አለ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ፕሮፌሰር ዓቢይ ይግዛውን እና ዶ/ር ቸሬ መስፍንን ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

ናይል፡- እነዚህን 15 ችግር ፈች ምርምሮች ሲያከናውኑ ያጋጠመዎት የማይረሳ ትውስታ ካለ ቢያጫውቱን?

አቶ ባየህ፡- በርግጥ የማልረሳው ትውስታ ከነዚህ ከአስራ አምስቱ ውጭ የሆነ ምርምር ሥሰራ ነው፡፡ በ2007 ዓ.ም የወረርሽኝ በሽታ ተነስቶ መንስኤውን ማወቅ ተፈልጎ ከ82 በላይ የበሽታው ተጠቂ ሰዎችን የሰገራ ናሙና ተወስዶ ሲጠና መንስኤው ከታወቀ በኋላ በሽታው በቁጥጥር ስር ዋለ፡፡ ነገር ግን የበሽታ አምጭውን ተዋሲያን በስፋት ማጥናት ስለፈለግን ወደ ምርምር ቀየርነውና በሽታ አምጭው ጀርም” በጥንቃቄ እንዲቀመጥ የቤተ ሙከራ ባለሙያው ተነግሮት ተቀመጠ፡፡ ከዚያ በኋላ የጥናቱን ውጤት ከኢንተርኔት ያነበበ ጣሊያናዊ ፕሮፌሰር በኢሜል የተቀመጠውን ጀርም ለምን በጣም ዘመናዊ በሆነ መንገድ ውስጠ ባህሪውን አናጠናውም ሙሉ ወጭውን ለ3 ወር እሸፍናለሁ ብሎ ተስማማን፡፡ ህጋዊ በሆነ መንገድ ባክቴሪያ ከሀገር ውጭ ለመውሰድ ሂደቱን ጀምሬ እያለሁ ጀርሙ በትክክል መኖሩንና በጥንቃቄ ማስቀመጡን በስልክ የቤተ ሙከራውን ባለሙያ ስጠይቀው ምን አለኝ መሰለሽ «አይ ተወግዷል» አለኝ ለምን? ስለው ቢሮ ስቀይር በአጋጣሚ ተወግዷል አለኝ እኔም ልምድ እወስድበታለሁ ያልኩትን አጋጣሚ አጣሁት፡፡

ናይል፡- ዩኒቨርሲቲው በአፍሪካ ካሉ አስር ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲው ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህንንም ለማሳካት ከተመራማሪዎች ምን ይጠበቃል?

አቶ ባየህ፡- ትክክል ነው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ የሚያስችሉ ስትራቴጂካዊ ዕቅዶችን አስቀምጧል፡፡ ስለዚህ የመምህራን የምርምር ተሳትፎ የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ አለበት፡፡ በስትራቴጅካዊ ግብ መሰረት በሚቀጥለዉ 5 ዓመት የመመህራን የምርምር ተሳትፎ 50% መድረስ አለበት የሚል ይመስለኛል ካልተሳሳትኩ፡፡ ነገር ግን በእኔ እምነት የምርምር ተሳትፎ በዩኒቨርስቲ ዉስጥ ግዴታ ነዉ፡፡ ስለዚህ መምህራን በየትምህርት ክፍሎች እና የምርምር ማዕከላት በከፍተኛ ሁኔታ መሳተፍ አለባቸው፡፡ በተጨማሪ ተመራማሪዎች በጋራ ከሀገር እና ከውጭ ሀገር ከሚገኙ ሰዎች ወይም ተቋማት ጋር መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ናይል፡- ዩኒቨርሲቲውን ለምርምር ምቹ ለማድረግ ምን መሰራት አለበት ብለው ያስባሉ?

አቶ ባየህ፡- በጣም ጥሩ፤ ምቹ የሚለዉን ቃል ከብዙ አተያይ ልንመለከተዉ እንችላለን፡ ምክንያቱም ለመመራመር ዋናዉ አስፈላጊ ቁልፍ ነገር ምንድን ነዉ ስንል? የመጀመሪያዉ የተረጋጋ የተማር የሰዉ ልጅ አእምሮ ማግኘት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የምርምር ግባቶች መሟላት ነዉ፡፡ ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው ትኩረት መስጠት ያለብት፡-

- ➢ ምቹ የአሰራር ወይም የአስተዳድራዊ ስራአት ማስፈን
- ➢ በተፈጥሮ ሳይንስና በሳይንስ ዘርፎች ደረጃውን የጠበቀ የምርምር ቤተ ሙከራ ማዘጋጀት
- ➢ ከሀገር ዉጭ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች ጋራ ግንኙነት መፍጠር
- ➢ በተለይ የተቋቋሙ የምርምር ማዕከላት ላይ ክትትል ማድረግና አቅማቸውን መገንባት
- ➢ ለምርምር በጣም ፈታኝ የሆኑ አሰራሮችን ለምሳሌ በምርምር በጀት አጠቃቀምና አወራረድ በተቻለ መጠን ለማቅለል በግልፅና አሰሪ የሆኑ የምርምር መመሪያዎችን ማዘጋጀት
- ➢ ለተመራማሪዎች የተጀመሩ ማበረታቻዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡ ይህ በብዙ ሀገሮች የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የሚጠቀሙበት ልምድ ነው፡፡

ናይል፡- በመጨረሻም ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለዎት?

አቶ ባየህ፡- ምርምር ለመሥራት በዝግጅት ላይ ላሉ መምህራን ማስተላለፍ የምፈልገው፡-

1. ደረጃዉን የጠበቀ የምርምር ግብአት እስኪሟላ ድረስ ምርምር ለመስራት አለመዘጋጀት ጥሩ አማራጭ ስለማይሆን ባለዉ መጀመር የግድ ነዉ፡፡ በተጨማሪ በጣም ጎበዝና ብሩህ ተማሪዎችን በምርምር ማስገባት ጠቀሜታዉ ብዙ ነዉ፡፡
2. የምርምር ሀሳብን ከማፍለቅ ጀምሮ እስከ ውጤቱ ድረስ በጋራ መሥራት፡፡
3. የተመራማሪ ዋና መገለጫ የሆኑትን የምርምር ስነምግባር (Ethics) እና ታማኝነት (honest) መከተል ጥሩ የአእምሮ እርካት ይኖረዋል የግል ምክሬ ነው፡፡
4. ችግር ፈች ምርምር ለመስራት የማህበረሰቡን ችግሮች በተገቢዉ መለየት መቻልና የቆራጥነት ወይም አልበገሬነት አቋም መኖር አለበት፡፡ ምክንያቱም ምርምር ጊዜን መስዋዕት ማድረግንና ታጋሽነትን ስለሚጠይቅ፡፡

ናይል፡- ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ስም በጣም እናመሰግናለን፡፡

አቶ ባየህ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# መረጃና የመረጃ ምንጮች ...

ከገጽ 7 የዞረ

የተሰራው ብቻ እንዳልሆነ አስረዱ፡፡ የተሰራው መጠኑ ወይም ቁጥሩ ተጨምሮ፣ ያልተሰራው ደግሞ እንደ ተሰራ ተደርጎ ሪፖርት እንደሚቀርብ ተናገሩ፡፡ ከሁሉም ዋናው ችግር ተብሎ የተወሳው ግን የሰሩትን አጋኖ ማቅረብ ማለትም ቁጥሩን ጨምሮ-ጨማምሮ ማቅረብ ነው - የዚያችን የፈረንጅ ላም የጥጃ ብዛትን አይነት፡፡

አንዱ የውይይታችን መርህ ማስረጃ ለሚሰጥ ሰው ቅድሚያ መስጠት ነው - እየተናገረ ያለውን አባል አቋርጦም ቢሆን፡፡ አንዱ አባል ድንገት "ኢንፎርሜሽን" በማለት እጅ አወጣ፡፡ "ተጨባጭ መረጃ ልስጣችሁ" ማለቱ ነው፡፡ እንዲናገር ተፈቀደለት፡፡ "ለምሳሌ የኛ አስተዳዳሪ የዞኑ የግብርና ስራዎች ሪፖርት ሲቀርብለት 'እዚህ፣ እዚህ ስራ ላይ ቁጥሩ አንሷል፣ ጨምሩበት' ይለናል፡፡ ከዚያ እንጨምርበታለን፡፡"

በመ/ቤቶች አካባቢ በተለይም ከእቅድ ሪፖርት ጋር በተገናኘ በመረጃዎች ላይ አላግባብ ጨዋታ የሚካሄደው ("የሚቆመረው" ላለማለት ነው)፣ "ጥሩ ሰርቻለሁ" በማለት ሽልማት ካለ ለመሸለም፣ ሹመት ካለ ለመሾም መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ወይም ቢያንስ-ቢያንስ ከተጠያቂነት ለመዳን ነው፡፡ ለዚህ አይነቱ የተጋነነ ሪፖርት አንዳንዶቹ የስራ ዘርፎች ይበልጥ አመች ናቸው፡፡ ሄዶ ለማየትና ለመለካት አመች አይደሉም - ለምሳሌ በአንድ ወረዳ የተከናወነ የእርከን ስራ በኪሎ ሜትር ርቀት ወይም የተተከለ ችግኝ ቁጥር ብዛት፡፡ እናም በአንድ ወረዳ ወይም ዞን ውስጥ በኪሎ ሜትር ተሰራ የተባለው እርከን ከመጋነኑ የተነሳ፣ "ከራሳቸው አልፈው አጎራባች ወረዳ ወይም ዞን ውስጥ ገብተው ሰርተዋል?" ሊያስኝ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል የተሰራውን ነገር መለካት አዳጋች ሊሆን ይችላል ወይም አሁን "በአካል" የለም - ለምሳሌ በጤና ተቋማት ለህሙማንና አስታማሚዎች የተሰጠ ትምህርት፡፡ አንድ የጤና ተቋም የህክምና ስራውን ከመጀመሩ በፊት፣ ደጁን የረገጡትን ሁሉ ወደ አዳራሽ በማስገባት ወይም ከወረፋ መያዢያ ቦታ በማስቀመጥ ስለመሰረታዊ ጤና አጠባበቅ ትምህርት ከሰጠ በኋላ እዚያ የተገኙትን በየቀኑ እየቆጠረ "አስተምሬያለሁ" በማለት ሪፖርት ሊያደርግ ይችላል፡፡ በቀጠሮ የመጡት፣ ያለፈውን ቀን ውጤት ለማወቅ የመጡት፣ በአስታማሚነት እዚያ የሰነበቱት፣ ወዘተ. ደግመው፣ ደጋግመው ይቆጠራሉ፡፡ አጅሬው ሪፖርት ግን በተደጋጋሚ የተቆጠሩትን ሰዎች የተለያዩ ሰዎች አድርጎ ይወስዳቸዋል፡፡ እናም የጤና ተቋሙ የወረዳውን ወይም የዞኑን ህዝብ አስተምሮ ያጋመሰ ወይም የጨረሰ የመሰለ ሪፖርት ይወለዳል፤ ነገሩ "በሬ ወለደ" ሆኖ ቁጭ፡፡

ከአመታት በፊት አንድ የአማራ ክልል የማስታወቂያ ቢሮ ሀላፊ ለክልሉ ጋዜጠኞች ስልጠና በሰጡበት ወቅት አንድ ነጥብ አነሱ - በመገናኛ ብዙሀን ዘገባ ላይ ቁጥር ስለመብዛቱ፡፡ አስታውሳለሁ - የመብዛቱን ነገር አምርረው ተቹ፡፡ ቃል በቃል እንዲህ ነበር ያሉት፤ "ህዝቡን ቁጥር እየመገባችሁት ነው"፡፡ መረጃው ሁሉ በቁጥር ተሞላ ማለታቸው ነው፡፡

በወቅቱ ከሀላፊው ሀሳብ ጋር የተስማማሁበትም፣ ያልተስማማሁበትም ነጥብ አለ፡፡ ጋዜጠኞች ዘገባቸውን በቁጥር እንዳያጥለቀልቁ የሙያው "ሀሁ" አበክሮ ያስተምራል፡፡ ዜናም ሆነ ሌላ የሚዲያ ዘገባ የስታቲስቲክስ ሪፖርት አይደለም፡፡ እርግጥ ነው፣ በሚዲያ ዘገባ ውስጥ፣ "ስንት?" ወይም "ምን ያህል?" የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት አንዱ ዋና ነጥብ ነውና መልሱ ይፈለጋል፡፡ ሆኖም ግን ሚዲያው ተደራሽ የሚያደርገው አብዛኛውን የሚዲያ ታዳሚ ነውና ቁጥር በማዥጎድጎድ የመረጃውን መልእክት ማደብዘዝ የለበትም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ታዳሚዎች ዋናው ጉዳያቸው ከቁጥሩ ላይ ሳይሆን፣ ቁጥሩ ከሚሰጠው ትርጉም ላይ ነው፡፡ እናም ቁጥር ሊዥጎደጎድባቸው፣ ቁጥር "ሊመገቡ" አይገባም፡፡ በዚህ ከሀላፊው ጎን ቆምኩ፡፡

ዋናው ነጥብ ግን ቁጥር መቀለቡ "ከምን መጣ የሚለው ነው?" እንደ ሀላፊው አመለካከት ከሆነ፣ የችግሩ ምንጭ ጋዜጠኞች ናቸው፡፡ በ'ኔ አመለካከት ደግሞ ዋናው የችግሩ ምንጮች ሀላፊዎች ናቸው - ቁጥርን ዋና የስኬት መለኪያ አድርገው የሚያቀርቡት፡፡ ለዚህ ማስረጃ አድርጌ ያቀረብኩት የ"ካምብሪጁ" ስልጠና ባልደረባዬ ያቀረበውን አብነት ነው፤ "እዚህ፣ እዚህ ስራ ላይ ቁጥሩ አንሷል፣ ጨምሩበት" የሚሉ ሀላፊዎች መኖራቸውን፡፡

ይህ ሲባል ግን በጋዜጠኞቹ በኩል ምንም ችግር የለም ማለት አይደለም፡፡ ሀላፊዎች እያጋነኑና እያንጋጉ የሚሰጧቸውን አሀዝ፣ የመረጃ ማስተላለፊያ ወንፊቱን ቀዳዳዎች በጣም በማጥበብ ማጥራት ሲገባቸው፤ እያግተለተሉ ማቅረባቸው፣ የቁጥሩን ትርጉም ማለትም በህዝቡ ኑሮ ላይ ያመጣውን ለውጥ መፈለግ አለመቻላቸው የብቃት ማነስ መገለጫ ነው፡፡ ዞሮ-ዞሮ ቁጥር የጥራትም፣ የእርካታም፣ ባጠቃላይም የልማት ማሳያ የሆነበትን የወቅታችንን ዘገባ ሲያዩ "ሰውዬው ምን ይሉ ይሆን?" እላለሁ፡፡

ከዚህ ሁሉ የከፋና አሁንም በስራ ላይ ያለ አንዳንድ ጋዜጠኞችና የተቋም (መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆነ) ሀላፊዎች ወይም ባለሙያዎች በጋራ የሚሰሩት የመረጃ ምንጮች ቁማር አለ፡፡ በዚህ አሰራር፣ ቁማሩ ያለው ከመረጃው ላይ ሳይሆን ከመረጃ ምንጮቹ ላይ ነው፡፡ እርግጥ ነው የመረጃ ምንጮቹ ቁማር የተፈለገው፣ ሀላፊዎቹና ባለሙያዎቹ አንዳንዴም ጋዜጠኞቹ ጭምር የሚፈልጉት መረጃ ብቻ በአይነትም ሆነ በይዘት ለህዝብ እንዲደርስ ለማድረግ ነውና ከመረጃ ምንጮች ቁማር የተገኘ መረጃ፣ ከመረጃ ቁማር ነፃ ሊሆን አይችልም፡፡ በእርግጥም የመረጃ ምንጮቹ ቁማር የተፈለገው፣ የመረጃ ቁማሩን ለማስገኘት ነው፡፡

አፈፃፀሙ እንዴት ነው? አንድ ጋዜጠኛ ወደ አንድ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ወዘተ. የዘገባ ተልእኮ ተሰጥቶት ወደ ቦታው ለመሄድ ከመንቀሳቀሱ በፊት በሙያው የተለመደውን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፡፡ ለሚሄድበት የዘገባ ጉዳይ ዳራ የሆኑ መረጃዎችን ይቃኛል፤ መቅረፀ ድምፅ፣ ካሜራ፣ ወዘተ. እንደ የሚሰራበት መገናኛ ብዙሀን ባህሪ ያዘጋጃል... ይህ ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ከመረጃ ምንጮች ቁማር ላይ የወደቀ ጋዜጠኛ ግን ገና ከሚድያው ደጅ እግሩን ሳያነሳ ከዚህ አልፎ የሚሰራው ተጨማሪ ተግባር አለ፡፡ ለዘገባ ተግባር ወደሚሄድበት ተቋም ስልክ በመደወል የመረጃ ምንጮችን አዘጋጅተው እንዲጠብቁት ይነግራል፡፡ ተገኘ ከተባለው ስኬት ተጠቃሚ የሆኑ ብቻ ሳይሆን ሀሳባቸውን አስተካክለው የሚገልፁ፣ አንደበተ ርቱእ የሆኑ ሰዎች (የመረጃ ምንጮች) ተመርጠው እንዲጠብቁት እንዲደረግ ይጠይቃል፡፡ ስራው ለሚዘገብለት ተቋም ይሄ ትልቅ እድል ነው፤ "ላሜ ወለደች" የሚያስብል፡፡ ተቋሙ ምኑ ሞኝ ነው፤ ጥሩ የሚናገሩና አፈ ጮሌ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን፣ የተጠየቁትን ቢጠየቁ ከተሰመረላቸው መስመር አንዲት "ኢንች" እንኳን ዝንፍ ሳይሉ የሚመልሱ "ታማኝ የመረጃ ምንጮችን" ያዘጋጃል፡፡

ጋዜጠኛውስ ምኑ ሞኝ ነው፤ ትክክለኛ የመረጃ ምንጮችን ለማግኘት ማን ደጋ ውጣ ፣ ማን ቆላ ውረድ (ብርድና ዝናብ፣ ሙቀትና ሀሩር ይፈራረቅብህ) አለው? ለምን መንገድ ይምታው? ስልኩን እስከ ደወለ ድረስ ከዘገባ ቦታው ሲደርስ የመረጃ ምንጮቹ በሰልፍ ተቀምጠው ያገኛቸዋል፡፡ የ'ሱ ድርሻ ጥያቄ ማቅረብ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ለአመል ያህል እንኳን ደንቀፍ ሳያደርጋቸው፣ አፋቸው ላይ ትንሽ እንኳን ጎርበጥ ሳይላቸው እያንተረተሩ ይመልሱለታል፤ ለዚያውም በልበ ሙሉነትና በፈገግታ ተሞልተው፡፡ አንዳንዱ የመረጃ ምንጭ የሚፈለገውን መረጃ በውል ከማወቁና ከመዘጋጀቱ የተነሳ ጋዜጠኛው ገና አንድ ጥያቄ እንዳቀረበለት የሚፈልገውን ሁሉ ሊነግረው፣ ሁሉንም ጥያቄዎቹን ሊመልስለት ይችላል - ምናልባትም ለራሱ ለጋዜጠኛውም በሚደንቀው ሁኔታ፡፡

የዚህ አይነቱ የመረጃ ምንጮች ቁማር ችግሩ ምንድ ነው? አንደኛ - አንድ ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው ፕሮጀክት ወይም የልማት ስራ ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ይኖራሉ፡፡ እነሱ ከዘገባው አይካተቱም፤ እናም በተመሳሳይ ተግባር ላይ የተሰማሩ አካሎች ከነዚህ ችግሮች ትምህርት ሳያገኙ ይቀራሉ፡፡ ሁለት - በፕሮጄክቱ ትግበራ ወቅት በተለያየ መንገድ እንቅፋት የፈጠሩ (አላግባብ ጥቅም ለማግኘት የሞከሩ፣ ስራውን ያደናቀፉ፣ ወዘተ.) ሳይጋለጡ ይቀራሉ፡፡ የጥፋታቸውን ያህል "ሳይቀጡ" ያመልጣሉ፡፡ ከዚህ አልፎም በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ የተሰማሩ ጥፋተኞች (ሙሰኞች፣ መልካም አስተዳደርን ደፍጣጮች፣ ወዘተ) ሳይቀሩ የልብ-ልብ ያገኛሉ፡፡ ሶስት - በፕሮጄክቱ ሂደት (በአስተዳደሩ፣ በባለሙያዎች፣ ወዘተ) ጎላ ያለ ቅሬታ ያላቸው ሰዎች ድምፅ ሳይሰማ ይቀራል፤ በፕሮጄክቱ ሂደት ውስጥ ድምፅ አልባ የሆኑት ዜጎች፣ በሚዲያውም ሜዳ ድምፅ አልባ ይሆናሉ ("በበደል ላይ በደል" እንዲሉ)፡፡ አራት - ይህ ሁሉ (ከ1-3 የተጠቀሰው) ተደምሮ፣ የሚዲያውን ተአማኒነት አፈር-ድሜ ያበላዋል፡፡ አምስት - የሚዲያውን አቀራረብ ምንችኬ (cliché) ያደርገዋል፡፡ ሁሉም የመረጃ ምንጮች በሁሉም ነገር አንድ አቋም ከመያዝና የፕሮጄክቱን መሪዎች ከማሞገስ አልፈው፣ የተጠኑ የሚመስሉ ቃላትና አረፍተ ነገራት ደግመው-ደጋግመው ሲያዥጎደጉዱ ፕሮግራሙ ልሙጥ ይሆናል - እጅግ አሰልቺ (monotonous)፡፡

መረጃ ያላቸው ተቋማት ከመረጃ ምንጮች ቁማር ውስጥ የሚገቡትስ ለምንድነው? ባጭሩ የሚፈልጉት መረጃ፣ ለዚያውም በሚፈልጉት መንገድ ብቻ ለህዝብ እንዲደርስ ለማድረግ ነው፡፡ እናም - ቀደም ሲል እንደ ተገለፀው - ወይ ይሾሙበታል ወይ ይሸለሙበታል፤ "ሚዲያ ያሾማል፤ ሚዲያ ያሽራል" እንዲሉ፡፡ ወይም ቢያንስ ተጠያቂነትን ከላያቸው ላይ ያርቃሉ፡፡ ስለሆነም የመረጃ ቆማሪዎች ለህዝቡ የሚነግሩት ስለስራቸው የተወሰነውን ገፅታ ብቻ ነው፡፡ እንዲሰማው የሚፈልጉትን የተወሰነ መረጃ በመስጠት የመረጃ "ሀብታም" ካደረጉት በኋላ እንዲሰማው የማይፈልጉትን የተወሰነ መረጃ በመንፈግ የመረጃ ድሀ ያደርጉታል፡፡ እናም የመረጃ ቁማር በመጫወት ህዝቡ ስለፕሮጄክታቸው ሊያውቀው የሚገባውንና ማወቅ መብቱ የሆነውን መረጃ በመንፈግ፣ የግል ወይም የቡድን ጥቅማቸውን ያስጠብቃሉ፡፡

የመረጃ ምንጮች ደገምገም አድርገው ወደ ሚዲያ ከቀረቡና የሚቀርቡበት ጉዳይም ተመሳሳይ ከሆነ ሚዲያ ላይ የመቅረብ ክህሎታቸውን ከማሻሻል አልፈው በሚዲያ የሚናገሩትን ጉዳይ እስከማሻሻል ሊደርሱ ይችላሉ፤ ማለትም የመረጃ ቃፊርነት (gatekeeping) ሚና ይጫወታሉ፡፡ ባለፈው አመት በመስክ ስራ ላይ የሰማሁት አንድ ቀልድ ለዚህ ጥሩ አብነት ነው፡፡ እዚሁ ጎጃም አካባቢ የሚገኝ አንድ አርሶ አደር የባዮጋዝ ተጠቃሚ በመሆኑ የቀበሌውም ሆነ የወረዳው አስተዳደር አይን ያርፍበታል፤ እውቅና ይሰጠዋል፡፡

በመሆኑም በመስኩ ላይ የሚሰሩ ተቋማትም ሆኑ ጋዜጠኞች ወደ አካባቢው ሲመጡ እንዲጎበኙት ያደርጋሉ፤ ስለስራው ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል፤ እንዲሁ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በአንድ ወቅት የወረዳ አስተዳደሪው ወደ ጽ/ቤቱ ካስጠራው በኋላ ከአንድ ጋዜጠኛ ጋር ያስተዋውቀዋል፡፡ ከዚያም ለጋዜጠኛው ስለባዮጋዝ ስራው ማብራሪያ እንዲሰጠው ይነግረዋል፡፡ አርሶ አደሩም የአስተዳዳሪውን ስም ከጠራ በኋላ፣ "ለጋዜጠኛው የምነግረው በመደበኛው ነው ወይስ በረገጣው?" በማለት ጠየቀ፡፡ "ስለአመላለሴ አቅጣጫ ይሰጠኝ" አለ ማለት ነው፡፡

"በመደበኛው" ከተባለ በባዮጋዙ ያገኘውን ትክክለኛውን የኤሌክትሪክ ሀይል መጠን ይናገራል - ማብራት የቻለው አንድ አምፑልም ይሁን ሁለት፣ ቡና ማፍላትም ይሁን እንጀራ መጋገር -

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ዕልቅናና መሪነት ...

ከገጽ 5 የዞረ

ማሳያ ነው። ይህ በራስ ውስጥ ሰላም እንዲነግስ በማስቻል መሪዎች ሙሉ አቅማቸውን ለመጠቀም የሚያስችላቸው መነሻ ነው።

ሦስት፡ መሪ መሆን ማለምን ይጠይቃል። አንዳንዴ ሠዎች ማለምን በስልጣን እርከኑ ጫፍ ላይ ያለው ሠው/መሪ ብቻ የሚከውነው ተግባር ሲያደርጉት ይስተዋላል። እርግጥ ነው ተቋማዊ መዳረሻ ሁሉም በየፊናው የሚስለውና በግሉ ተሸክሞ የሚጓዘው አይደለም። ሁሉም የተቀበለው፣ የተረዳውና ለስኬቱ የሚተጋለት የመጨረሻ ተቋማዊ ውጤት መኖር የግድ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉም ባለበት እርከን የሚመራውን ቡድን/ዘርፍ መዳረሻ ማለሙ የግድ ነው። ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ዓ.ም. በአፍሪካ ካሉት 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች መሆንን ሲያልም በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎት ምርጥ ይሆናል ማለት ነው። ነገሩ እዚህ ላይ ሊቆምም አይችልም - የፋይናንስ፣ የሠው ኃይል ልማትና አስተዳደር፣ የአይ ሲ ቲ፣ የተግባቦትና አጋርነት፣ የገቢ ማመንጫ፣ የሃብት አጠቃቀምና አስተዳደር፣ . . . ወዘተ ሁሉ ምርጥ በሚባል ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ማለት ነው። በመሆኑም በነዚህ ዘርፎች ሁሉ ያለው አመራር ዩኒቨርሲቲያችን ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን የኛ ዘርፍ ቁመና ምን ሊሆን ይችላል ብለው ማሰባቸው የግድ ነው ማለት ነው።

አራት፡ መሪነት በስጋትና በፈተና የታጠረ ለሌሎች የሚሰጥ አገልግሎት ነው። ፈተናውን ለመሻገር ደግሞ ችግሮችን መጋፈጥና ውጤታቸው ላይ እርግጠኛ መሆን የማያስችሉ ውሳኔዎችን ደፍሮ መወሰን እና ውጤቱን መቀበል ይጠይቃል። ፈርቶ መምራት አይቻልም። የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ውጤትን በመተንበይ መወሰን የመሪነት ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

አምስት፡ መሪዎች ባሉበት ሠፈር ግርግርና ውዝግብ የሚጠበቅ ነባራዊ ሁኔታ ነው። ክርክር፣ እሺታና እምቢታ ይህንን ተከትሎም ምስጋናና ርግማን አቤቱታና ክስ . . . የሚፈራረቅበት ሠፈር ነው። ታዲያ መሪዎች በየሰዓቱና በየዕለቱ አዲስ ጉዳይ ፊታቸው ዱብ ሲል የማይደነግጡ እንዲያውም አዲስና ያልጠበቁት ጉዳይ ሲያጋጥማቸው እሱን ተከትሎም ግርግርና ውዝግብ ሲከሰት ከመጤፍ ሳይቆጥሩ በተረጋጋ መንፈስ ውስጥ ሆነው ሌሎችን የሚያረጋጉ ናቸው። አልፎ ተርፎም ከአዲሱ ዱብ ዕዳ የሚጠቅማቸውን መዘው በመውሰድ ለዕቅዳቸው ስኬት የሚጠቀሙ ናቸው።

ስድስት፡ መሪዎች በተሰማሩበት ዘርፍ የሚመጣውን ውጤት ባለቤት በመሆን ይቀበላሉ። ስኬት ሲሆን ግንባር ቀደሞችን ለይተው የሚያሳዩ ሲሆን ለውድቀት ግን በራሳቸው በኩል የጎደለውን ነቅሰው ለማረም ይተጋሉ እንጂ ምክንያትና የናቴ ቀሚስን ሲያፈላልጉ አይገኙም።

እና እርስዎ ከነዚህ ውስጥ የትኛውን ይመስላሉ? መሻሻልስ እንዴት እንደሚችሉ አስበውና አቅደው ያውቃሉ? አሁን ያለንበት ዘመን በየዕለቱ መማርን የሚጠይቅ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። ትምህርት ደግሞ እስኪሞቱ ነውና የጎደለን በመለየት ከልምድ፣ ከመጽሃፍት፣ ከመደበኛ ትምህርትና ከሌሎች በመማር ራሳችንን እንገንባ ነው የዛሬው መልዕክት።

# መረጃና የመረጃ ምንጮች...

ከገጽ 10 የዞረ

ሀቁን ያስቀምጣል። "በረገጣው" ከተባለ ደግሞ እያበራ ያለውን የአምፑል ብዛት በሁለት ወይም በሶስት እጥፍ በማሳደግ፣ ለጎረቤቶች መብራት እንዳከራየ ሁሉ በመጥቀስ፣ ወዘተ ያስረዳል ማለት ነው።

ቀልዱ መቶ-በመቶ ይሆናል ባይባልም፣ ቢያንስ-ቢያንስ በመረጃ ምንጮች ቁማር አንጀታቸው ያረረ መረጃ ተቀባዮች (የሚዲያ ታዳሚዎች) እንደ ፈጠሩት መገመት አያዳግትም። አንድ መረጃ ለህዝቡ ሲደርስ፣ የተሰወኑ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን ጥቅም በሚያስከብር መልኩ ተቀርፆ እንዲቀርብ ሲደረግ እንዲህ የሰውን አንጀት ያበግናል። ከብግነቱ የሚወጣው ትንፋገን ደግሞ እንዲህ መሰል ቀልዶችንና ስላቆችን አርግዞ ይወልዳል።

ያም ሆነ ይህ ለሙያው ስነምግባር ሙሉ-በሙሉ የተገዛ ጋዜጠኛ ከፍ ሲል ከቀረበው አይነት የመረጃ ምንጮች ቁማር ላይ እንደማይወድቅ ግልፅ ነው። በአንድ የሚዲያ ስነምግባር ትምህርት የክፍል ውይይታችን ወቅት ከአንድ ተማሪዬ የተነሳ ምሳሌ እዚህ ላይ ጥሩ አብነት ነው። ጋዜጠኛው የአማራ ክልል መገናኛ ብዙሀን ከሚያስተዳድራቸው ሚዲያዎች (ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን ወይም ጋዜጣ) ውስጥ ለአንዱ የሚሰራ ነው። ለመስክ ስራ ወደ ወረዳ ይሄዳል። በግብርና ስራ ውጤታማ የሆኑ አርሶ አደሮች ጋር እንዲያገናኙት ይጠይቃል፤ አቀረቡለት።

ከአንዱ አርሶ አደር ጋር ቃለ ምልልስ ሲያደርግ፣ አርሶ አደሩ በግብርና ስራው ውጤታማ ከመሆኑ የተነሳ ኑሮው በከፍተኛ ደረጃ መቀየሩን ከመግለፅም አልፎ ስላፈራቸው የቤት ንብረቶች ሳይቀር ይዘረዝራል፤ በባንክ ብር ማስቀመጡን ጭምር ያስረዳል። ጋዜጠኛውም ቆቅ ነበረና ወደ ቤቱ እንዲወስደው ይጠይቀዋል፤ ተያይዘው ይሄዳሉ። የአርሶ አደሩ ቃልና ከቤት ውስጥ የሚታየው ሀቅ አራንባና ቆቦ የሆነበት ይህ ጋዜጠኛ የነገረውና አሁን በአይኑ የሚያየው ለምን እንደ ተለያየ ይጠይቀዋል። አርሶ አደሩም፣ "እንደዚያ ብዬ እንድነግርህ የምትፈልግ መስሎኝ ነው" ብሎት እርፍ።

ከመግቢያችን አካባቢ እንደ ተጠቆመው ያለ መረጃ እውቀት የለም፤ ትክክለኛ እወቀት፣ ከትክክለኛ መረጃ እንደሚገኝ ሁሉ፣ የተሳሳተ እውቀት ከተሳሳተ መረጃ ይመነጫል። በመረጃ ላይ የሚፈፀም ቁማር፣ የሌለ ወይም ያልተከሰተ ነገር ከመፈብረክ አንስቶ ሀቁን የራስን ጥቅም በሚያስከብር መንገድ እስከ መበረዝ ይደርሳል፤ የመረጃ ምንጮችን በተለያዩ ጥቅሞች በመደለል የእውቀትን መሰረት ያበላሻል። በትክክለኛ መረጃ ላይ ያልተመሰረተ እውቀት ደግሞ አደገኛ ነው - ሰዎችን ለተሳሳተ ውሳኔ ያበቃቸዋልና። አንዳንዱ በመረጃ ላይ የሚከወን ቁመራ በአይነቱም፣ በአቀራረቡም ረቀቅ ያለ፤ በጣም ገባ-ጠለቅ ብለው ካላዩት ሊደረስበት የማይችል ሊሆንም ይችላል። ለዚህ አይነቱ ቁመራ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን የንግድ ማስታቂያዎች ናቸው። ኢንሻ አሏህ የነሱን ነገር በሌላ ጊዜ እንመለስበታል። ቸር እንሰንብት!

# ፍልስፍናዎቻችን

አትክልት ዳኛው የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ግቢ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ባለሙያ

የሠው ልጅ አዕምሮ በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ሀሳቦችን ያመርታል። በአብዛኛው ያለፈውን በማጠንጠን የተጠመደ ነው። እኔም ሰው እንደመሆኔ ደጋግሜ የማጠነጥነው አንድ ማህበራዊ ምልከታ አብሮን እንቃኝ። እናንተንም፣ እኔንም ይመለከተናል። ነገሩስ አለባበሳችን ነው። ለምንድን ነው ስለ አለባበሳችን ይህን ያህል የምንጨነቀው? የሚለውን ሃሳብ ከራሴ አልፎ ጓደኛዬን ጠየቅኩት። መቼም ጓደኛ ጊዜን ብቻ ሳይሆን በአመዛኙ ስሜትን የሚያጋሩት ውስጥ-አወቅም አይደል! ጓደኛዬ ጥያቄው ምንም አስቦበት የሚያውቅ መሆኑን በሚያሳብቅ ስሜት ‹ያው ውብ ሆኖ ለመታየት ነዋ! ለመዘነጥ› ብሎኝ እጆቹን አወናጭፎ ተወኝ በሚል እንቅስቃሴ መለሰልኝ። ጥቅል በመሆኑ ብዙ አላረካኝም። እሱን ግን ከዚህ በላይ መጠየቅ አልፈለኩም።

ለዚህ ጥያቄዬ ከረጅም ጊዜ በኂላ በአንድ ጉዞ የሁለት ወጣቶች የሞቀ ክርክር የተሻለ ነው የምንለውን መልስ ሠጥቶኛል። ነገሩ እንዲህ ነው። አንድ ቀን ከፍተኛ የመኪና መጋፋት ባለበት የአዲስ አበባ ጎዳና ታክሲው በየቅርብ ርቀቱ እየቆመ ትዕግስት አስጨራሽ በሆነ ፍጥነት ያዘግማል። በል ሲለውም በአንድ ቦታ ለብዙ ጊዜ ይቆማል። በዚህ ቅፅበት ከመጠን በላይ ተሽቀርቅራ የለበሰች ወጣት ስታልፍ ብዙ አይኖች ተከተሏት። የወንዶች ብቻ አይደለም እንዲያውም የወጣት ሴቶች እይታ ራሳቸውን በእሷ ልብስ ብንሽቀረቀር ምን እንመስል ይሆን; የሚል አይነት ነበር። ይህን ለማለት ያበቃኝ እሷን ካዩ በኂላ የራሳቸውን ልብስ በማስተዋል ከእሷ ጋር ሲያነፃፅሩ ያየኂቸው ስለነበሩ ነው። ወጣት ወንዶች ደግሞ ቀሚስ ገለብ በሚባል እይታ ስንመለከት በተለይ ከኂላ የነበርን ሶስት ወጣቶች አንገታችንን አስግገን፣ አንዳችን ባንዳችን ተደራርበን፣ አንገታችንን ብቻ ከመኪና ለመስወጣት የፈለግን በሚመስል አኳኋን ከአይናችን እስክትሠወር ሸኝተናት ስንመለስ አይተኸዋል በሚል መገረም ባለበት ምልክት ቋንቋ ተግባብተን በድርጊታችን ሀፍረት የተቀላቀለበት ፈገግታ ተለዋወጥን። በመካከላችን የተቀመጠ ጥርሱ ከመጠን በላይ የነጣበት ጠይም ወጣት ‹መጽሐፍን ሽፋኑን በማየት ብቻ ውስጡን ሳታይ አትተች›› ውጫዊ አለባበስን ሳይሆን ውስጣዊ ውበትን (ርህራሔን፣ ፍቅር፣ ለሌሎች መኖር፣ ቀና አስተሳሰብን ወዘተ...) በማየት ነው መገመት የሚገባህ በማለት ምክር ቢጤ ጣል አደረገለት። እኔንም ሊጨምር እንደሚችል ገመትኩ።

ከመስኮቱ ጥግ ቁጭ ያለው ባለመነጽር ወጣት |‹ንግግርህ ያስቃል አንተ ራስህ እኮ አይንህን ጎልጉለህ ስታይ አልነበር? ከመቼው መካሪ ወጣህ› በማለት የስላቅ ሳቅ እያሳቀ በትዝብት እይታ ገረመመው። የመጀመሪያው ጠይም ልጅም ‹አየህ አንተ ስለ ልብስ ትርጉም ጠለቅ ያለ መረጃ ስለሌለህ እኮ ነው› ብሎ ሳይጨርስ ባለመነፀሩ ልጅ ‹ቅድም ስለ መፅሐፍ እና ሽፋኑ የነገርከኝ ምሳሌ ከብዙ ዓመት በፊት እውነትነት ያለው አባባል ነበር። አሁን በዚህ በካፒታዝም ዘመን ገንዘብ የኃይል ሁሉ ምንጭ ተደርጎ በሚቆጠርበት ዘመን ምን አለው እንጂ ምን ማበርከት ይችላል? ብሎ የሚመዝንህ ያለ እንደሚመስልህ መፅሐፍን ጥሩም መጥፎም ላልከው እንኳን ፀሐፊዎቹ አሁን አሁን ከይዘቱ ይልቅ ለርዕሱ እና ለሽፋኑ ቀለም አብዝተው መጨነቅ ጀምረዋል። ለምን ይመስልሃል? ሰው ውስጡን ከማየት ይልቅ ሽፋኑን ማየት ስላዘወተረ ነው። ወደው እንደይመስልህ። እናማ ወዳጄ እንደዘመኑ ለመኖር የሚለውን ፈሊጥ ተከታይ ከሆንክ ውስጥህን ከማስዋብ ይልቅ ላይህን ማስጌጥ በሰዎች ጥሩ ሆነህ እንድትነበብ እድል ይሠጥሃል። መነበብ የምትፈልግ ከሆነ ማለቴ ነው። እስኪ የተጨመታተረ እና የቆሸሸ ልብስ ለብሰህ በከተማዋ ጎደናዎች ተዘዋውርና ሞክረው። ምን ያህል ሰዎች እንደሚያስተውሉህ ታዘብ። ለብዙ ሰዎች ስትዞር ብቻ እንደምትቀፋቸው ታስተውላለህ። አይን አይከለከል ሆኖባቸው በስህተት (በአጋጣሚ) ተመለከቱህ ካንተ አይናቸውን ለመንቀል የሚደርጉትን

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# The Need to Inspire Civic Virtue and Build Good Moral Character Traits in the Young Generation of Ethiopia

Chalachew Tarekegne (PhD Candidate) (Department of Civics and Ethical Studies)

**Introduction**

*"Is there no virtue among us? If there be not, we are in a wretched situation. No theoretical checks, no form of government, can render us secure. To suppose that any form of government will secure liberty or happiness without any virtue in the people is a chimerical idea"…*
***James Madison***

Ethiopia's commitment to inalienable rights, the cornerstones of democracy, requires each citizen to uphold those rights for all others. Citizenship in such a diversified society is defined not only by an affirmation of democratic first principles, but also by a willingness to engage in civil debate and to work for public policies that serve the common good.

Preserving, expanding and consolidating democracy was a challenge for each succeeding generation in Ethiopia. No profession plays a more central role in meeting this challenge than the civics and ethics teachers in our country's schools and universities. At the heart of civics and ethics is the obligation to teach Ethiopian values and democratic principles and to inspire civic virtue in the young people who will shape our better future. The aim of this paper is to call for action in the kindergartens, juniors, high schools and universities of Ethiopia that will inspire civic virtue and build moral character traits in the Ethiopian youth.

It is not difficult to identify threats to the fundamental ideals and values of Ethiopia that had survived long lasting century. It is getting common knowledge to observe violence incidents in the universities of Ethiopia; it is common knowledge to hear about some university students' prostitution and abortion practice, it is also common knowledge to observe exam cheating in both university and high school students. It is also experienced to listen noisy music sounds while teaching in the universities. Today, egoism or extreme selfishness is getting rampant and free ridding is considered as civilized thinking. Among youth today,though there is awareness to some extent, knowledge and understanding of the Ethiopian values and the principles of the democratic system of government are not still possessed by them very well. It is clear that young people are gettingincreasingly indifferent to civic affairs. How is it possible to ensure sustainable development and consolidate democracy if the youth are getting indifferent to civic affairs?

### Inspiring Ethiopian values, democratic principles and ideals

In a society such as ours, where citizens are diverse, it is essential that schools, universities and communities foster a reasoned commitment to the founding principles and values that bind us together as a people. A commitment to the restoration of Ethiopian values, practice of democratic principles, a willingness to engage in the democratic process, and the inspiration of core values are key elements of the bond that joins us as "we the people" today. There are opportunities to debate over differences though our debating culture is poor. The spirit of our nation also requires the inspiration of our civic virtues (toleration, civility, public-spiritedness, trust, impartiality, compromise, diligence, patriotism, among others) for a commitment to these principles and values is the foundation of the sense of civic virtue which is so essential to the well-being of our country and to ensure democratic governance in the country at large.

**The teaching of good moral character traits also requires that schools and universities create positive links with parents and community members as well as religious institutions, and the media.**

The citizen must demonstrate a reasoned commitment to fundamental principles, such as popular sovereignty, rule of law, freedom of association, and the like. The citizen must also demonstrate a reasoned commitment to fundamental values, such as life, liberty, pursuit of happiness, equality, justice, truth, and promotion of the common good (give priority to public- interest than self-interest.). The students should explore Ethiopian values, understand the nature of democratic principles and demonstrate a commitment to those values and principles in the daily activities of their private and public lives.

Civic education is not complete until students possess a set of appropriate civic dispositions. Civic dispositions are those habits of the heart and mind that are conducive to development of virtuous citizens and emergence of healthy state (Aristotle, Machiavelli). The civic dispositions which include civility, open- mindedness, compromise, and toleration of diversity, among others are perquisites of a civics life in which the Ethiopian people can work out the meanings of their values and principles of ordered society where social justice prevails.

### Civic virtue and civic education

The need to build character traits and civic virtues must be a critical task for our country's schools and universities. Mostly, it is an often misunderstood and neglected component of the school curriculum. Traditionally, it is to be noted that civic education has consisted of three components: first, the development of knowledge and understanding about the democratic institutions and principles and their history; second, the development of the intellectual and participatory skills necessary for competent participation in the democratic process and standing for justice; and third, the development of an appreciation for democratic values and principles that result in the civic dispositions essential for a vital civic life. This third component of civic education is closely related to the development of what we call civic virtue.

According to French political philosopher, Alexis de Tocqueville, civic virtue refers "habits of heart," that is, a commitment to democratic principles and values that manifests itself in the everyday lives of citizens. A focus on knowledge and skills alone is insufficient for the task of civic education. Civic education must also foster the inculcation and development of civic values which will bring the society towards common bond.

It is also to be noted that good moral character traits building is a complex process. An essential, and often neglected, dynamic of character traits formation is the provision of opportunities for students to observe and practice good character traits development and civic virtue. In other words, homes, schools, universities, communities, and religious institutions must be places where the children, the young and adults model good moral character trait building and each of them have the opportunity to live out the ideals of good moral character traits and citizenship. Civic virtue must be lived, not just studied. Plato, in his notable book the *Republic* stressed the importance of possession of civic virtue and national values by the young generation. He remarkably noted "nothing bad moral influence should reach the young." He emphasized the significance of censoring art as "*Let me write the ballads of the country and I care not who write the laws of [Greek]*". According to him, enabling the young generation possess civic virtue is not going to be achieved by formulating *Good Laws of the country [Greek]*. Instead, we can enable the young possess civic virtue by editing the messages art works like drama, theatre, and film are transferring to the youth. And accordingly, therefore, we need to be careful to author the thematic contents of art works delivered to the kids, students and the youth in general. We need also to control the messages transferred by art works if they have the potential to damage the youth. Viewed from Platonic Art Analysis, I

continued on page 13

# The Need to Inspire Civic Virtue ...

continued from page 12

feel that we Ethiopians are the looser since; particularly, uncontrolled video houses are supplying films with pornographic content which are abusing students from kindergartens to university level. Alas!

This is not to say that the present Ethiopian educational curriculum does not enrich students with the required good character traits and civic virtue. Yet, it is plausible to suggest that the inspiration of Ethiopian values provides the necessary conceptual framework for an understanding and appreciation of the democratic ways of life and promotion of non- violence and social harmony. The attention to such kind of concern can also be a rich source of attractive examples of the protection and enrichment of our democratic way of life which can be achieved through the practice of civic virtue and building of good moral character traits.

Thus, teaching academic subjects and building moral character traits can be mutually reinforcing tasks. *Intellectual virtues* such as*logical reasoning, formulation of scientific principles, and contemplation* and *moral virtues* such as patience, diligence, responsibility, reflectiveness, and honesty are critical to the development of each student's intellectual and moral excellence. In other words, the teaching of personal virtues is often a contribution to the development of civic virtue. To teach academic subjects well is also to teach certain virtues relevant to personal and civic life. From this point of view, each subject matter teacher has to possess civic virtue and build his own good intellectual and moral character traits to demonstrate modeling effect to the students s/he taught.

It is inadvisable to make sharp distinctions between private and public virtue and between teaching academic subjects and teaching moral character traits (civics and ethics). For example, a person possesses the personal virtue of honesty when that person can be counted on to be consistently honest in dealings with others. A person possesses the civic virtue of respect for the worth and dignity of others when he or she can be counted on to behave in a manner consistent with that value. It clear, however, that honesty and respect for others are relevant to both civic and private life.

Education that provides students with a rich knowledge and understanding of their responsibilities as citizens in a democracy must be accompanied by opportunities for students to develop the civic dispositions to act virtuously on their private and public lives. Many young people today have somehow adequate knowledge of their civic responsibilities, but fail to live out (governed by) these ideals. For example, in Ethiopian universities and high schools, students know about the social and economic crises engendered by HIV/AIDS. Unfortunately, there are still some students who have the potential to be exposed for it. Frankly speaking, the present Ethiopian generation (especially the young) are robbed of his/her innocence because of cultural globalization or cultural pollution. What is essential, therefore, is to expose the young generation of Ethiopia to indigenous models of civic virtue and to provide the opportunity to practices these civic virtues in a meaningful and rewarding manner. Communities, schools, universities and religious institutions need to recognize the different learning processes shaping the civic "habits of the heart."

## The Role of the Ethiopian Community, Religious Institutions, the Schools and Universities in Building Good Moral Character Traits and Civic Virtue

The task of building good moral character and inspiring civic virtue is not the exclusive area of social sciences studies even though it falls most directly in social sciences professionals. It can also be preached by the hard sciences professionals. One precondition is a school and university environment consistent with the principles. Students' lives in schools and universities should be based on fundamental Ethiopian values and the practical application of these values .

Careful attention to the schools and universities culture is critical if schools/universities are to strengthen the development of good moral character traits and civic virtue. The curriculum of the schools/universities has the potential to teach important lessons about toleration, diversity, respect, trust, honesty, accountability, among others. The principles and values underpinning the day-to-day operations of the schools and universities should be consistent with the values taught to young people.

Schools and universities should be places where clear expectations for student conduct exist and are firmly and fairly enforced. The expectations placed on students in schools/ universities, as well as the behavior of teachers, should be informed by basic democratic principles and core Ethiopian values. Schools should also provide opportunities for young people to practice civic virtue. Students should be encouraged and given the opportunity to make positive contributions to the well-being of fellow students and to the school/universities.

Teachers in schools and universities need to give serious attention to good moral character building and bear a special responsibility for their own conduct, too. One important dynamic by which individuals acquire values is through exposure to attractive models of behavior. School/university curriculum that attempts to teach values such as toleration, trust or respect is unlikely to be successful in the hands of teachers/lecturers who are irresponsible in the performance of their professional duties and disrespectful in their dealings with students. Likewise, a school/ university is unlikely to help students' sense of justice when discipline or grading procedures are perceived by students as unfair.

The teaching of good moral character traits also requires that schools and universities create positive links with parents and community members as well as religious institutions, and the media. Parents should participate in the dialogue over the values that schools and universities will offer and should reinforce those values in the home. Mass media has to disseminate those model character traits that will add value to the collective well-being of the Ethiopian community.

Consistency of effort is very important. The community, including religious leaders and the media should also cooperate with parents, schools and universities. Historical and cultural differences between communities may well result in differences in approach to civic education and the development of civic virtue. Such differences are a natural consequence of our national bondage and should be treated accordingly. Acknowledging this is not, however, an endorsement of moral relativism or situated ethics. Good character traits and civic virtue must follow democratic procedures, involve all community stakeholders, and result in practices that are consistent with the democratic principles and values as enshrined in both national and international documents.

Finally, all those involved with young people should inspire the importance of good moral character traits and good citizenship (virtuous citizen). Schools, universities, religious institutions, and the media should recognize and reward students who display good moral character traits and civic virtue. Recognition and rewarding programs should be established in schools, universities and the community centers and featured by local and national media.

## Good moral character traits education and the introduction of civic virtue: across the curriculum approach

The methods used to build good moral character traits and civic virtue will vary in some respects depending upon the community and grade level of the students. The fundamental position of all teachers and university lectures, however, should be that there is a common tradition (core Ethiopian values) worth preserving and transmitting to the present and next generation of Ethiopia.

In the kindergartens and juniors, teachers must focus on basic social skills and the development in children of habits such as toleration, civility and self-discipline that are necessary for working successfully with others. At the secondary schools and university levels, there should be an increasing emphasis on the development of a mature understanding of the fundamental principles of our shared civic life (values) and their history, their importance to strengthen social bond and social trust as well as on the civic dispositions and skills needed to engage in the public debate over the practice of these principles.

All high school teachers and university lecturers, along with other educators, administrators, community leaders, and concerned stakeholders must promote good personal character traits in their classrooms, schools and universities. This will involve clear specification of the nature of good

continued on page 14

# The Need to Inspire Civic Virtue ...

continued from page 13

character: rewards for its display; awareness by teachers of the character they reveal to students; and alertness to opportunities to promote good character traits through the dynamics of the classroom, school and university climate.

### Conclusion

This position statement calls for the need to give a new lease of life to the core traditional values of Ethiopia and civic virtues to be acquired by the young generation. For the revitalization of good character traits and production of virtuous sprit in the citizens at large, untiring effort is needed from the general public, educators, schools, universities , communities, religious institutions , policy makers, and the media. This is a critical time in the history of Ethiopia when the *social fabric* that binds us as a people for three thousand years (or 4500 years as cited in Encyclopedia Britanica, 1994 by implication) appears to be weakening and deteriorating. Especially, the schools and universities all over the country have a critical role to play in the revitalization (inspiration) of the fundamental Ethiopian values and civic virtues to sustain the *social bond*s and *civic engagements* we have had.

The development of civic virtues and good character traits in the young people of Ethiopia requires much more than traditional didactic methods of instruction. The cognitive outcomes of education are vital, but good character trait is not formed only on the basis of the study of traditional subject matter. Although subject matter is an essential component of the reflective process that leads to a mature understanding of the nature of civic life, the focus of education needs to be widened to encompass the quality of the civic experiences that classrooms, schools, universities, and communities provide to students also.

University and high school teachers have a responsibility and a duty to refocus their classrooms on the development of good moral character traits and civic virtues. They should not be hesitant about working toward these grand goals. The fate of the country to ensure sustainable development and consolidate democratic governance depends to a large extent on the renaissance and renovation of civic virtues that resides in the Ethiopian society and rejuvenation of core Ethiopian values that promote toleration, civic engagement, social capital, and social harmony. The high schools and universities of this country has a vital role to ensure the renaissance of lost Ethiopian social fabrics that tighten the bonds of the society for centuries and revitalize the civic virtues deem necessary to consolidate social harmony and *ahimsa* (non-violence).

After all, teachers at all levels, are the defenders of Ethiopian core values and the national guards to challenge cultural globalization(pollution). Otherwise, as has already been stated by Madison in the introductory part, to think of democratic governance and sustainable development while citizens' are living without civic virtue is a chimerical idea. Because, ultimately, the strategic actor of democratic governance and sustainable development is the virtuous human resources (VHRs).

# ፍልስፍናዎቻችን ...

ከገጽ 11 የዞረ

ጥድፊያ ስታጤን ተመልካቾችህ ምን ያህል እንደሚሸማቀቁብህ ይገለጥልሃል፡፡ ተመልካች ከሌለህ ደግሞ አንተ በራስህ ብትኖርም እንኳን በሰዎች ዘንድ እየኖርክ አይደለም፡፡ አንተ ወደ እነሱ ሄደህ ብታያቸው ወይም ጮኸህ እንዲያዩህ ብታደርግ እንኳ በሙሉ አይናቸው ስለማያዩህ ወይም ከንፈራቸውን መጥጠው እና ተፀይፈው ስለሚያዩህ አዩህ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ጠቅለል ሳደርገው መነበብ ከፈለክ ሽፋንህን ጥሩ አድርገህ ልትስባቸው ይገባል ያ ካልሆነ ግን ወደ አንተ አይሳቡም፤ ካልተሳቡ ደግሞ አያነቡህም፡፡ ካላነበቡህ ደግሞ አንተ በነሱ ውስጥ የለህም (አልኖርክም)፡፡ ይህ ሃሳቤ የበለጠ እንዲገባህ አንድ የሱፊዎችን ታሪክ ጲላጦስ ከተረጎመው ላስታውስህ፡- አንድ ቀን የእስራኤል ልጆች ወደ ሙሴ ተሰብስበው መጥተው እግዚአብሔርን እራት ሊጋብዙት እንደሚፈልጉና ይህንኑም እንዲነገርላቸው ሙሴን ጠይቁት፡፡ በዚህ የድፍረት ጥያቄ የሙሴ ቁጣ ነደደ፡፡ ‹‹ እግዚአብሔር የሰውን ምግብ አይመገብም፤ ወደ እናንተ የራት ግብዣ እንዲመጣ ማሰባቸሁም ሞኝነት ነው›› አላቸው፡፡ የእስራኤል ልጆችም እያዘኑ ተመለሱ፡፡ በነጋታው ምሽት ላይ ሙሴ እንደለመደው ከእግዚአብሔር ጋር ሊነጋገር ወደ ተራራ ወጣ፡፡ በተራራው ጫፍ ላይ ሲደርስ እግዚአብሔርም ‹‹ባሪያዎቼ የእራት ግብዣ አድርገውልኝ ለምንድን ነው አሳፍረህ የመለስክብኝ በማለት በሀዘን ጠይቀው፡፡ ሙሴም ጌታ ሆይ! የሰው ምግብ አትበላም ብዬ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱን የሞኝ ግብዣም አትቀበልም የሚል እምነት አድሮብኝ ነው›› አለ፡፡ እግዘአብሔርም አዘዘው ‹ሂድና ለህዝቤ ንገረው፡፡›› ነገ ማታ ለእራት እመጣለሁ፣ ግብዣቸውንም ተቀብየዋለሁ...›› ሙሴም በሌሊት ወደ ህዝቡ ተመለስ እግዚአብሔር የእራት ግብዣቸውን እንደተቀበለ አበሰራቸው፡፡ ‹‹ማታ እራት ከእናንተ ጋር ነኝ፣ ተዘጋጁ ብሏል›› አላቸው፡፡ ህዝቡም ድግሱን ማዘጋጀት ጀመሩ፡፡ በእስራኤል ምድር ታላቅ የተባለው ግብዣም መሰናዶው ወደ መጠናቀቁ በተቃረበበት ሰዓት አንድ በረሀብ የከሳና የቆሸሸ ልብስ የለበሰ ሽማግሌ ድንገት ወደ ድንኳኑ ደጃፍ ተጠግቶ "እባካችሁ ተርቤያለሁ ... ከድግሱ የምበላው ትንሽ ስጡኝ ..." በማለት ልመና አቀረበ፡፡ ህዝቡ ግን እያዳፉና እየገፈታተሩ አስወጡት "እኛ የደገስነው ከእግዚአብሔር ጋር ለመብላት ነው በማለት አባረሩት፡፡ የዚያን ቀን ማታ እግዚአብሔር ሳይመጣ ቀረ፡፡ ሙሴም እጅግ አፈረ፤ ብዙዎቹም ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግሬ መጣሁ የሚለን ሐሰት ነው በማለት ጠረጠሩት፡፡ በበነጋታው ምሽት ላይ ሙሴ በሲናይ ተራራ ወጥቶ እግዚአብሔርን መጠበቅ ጀመረ፡፡ እግዚአብሔርም በሰዓቱ መጣ፡፡ ሙሴም በሐዘን ‹‹ጌታ ሆይ! የእራት ግብዣቸውን እንደተቀበልክ ለህዝብህ ነግሬ ነበር፡፡ አንተ ግን ቀርተህ አሳፈርከኝ አለ፡፡ እግዚአብሔርም ‹‹ሙሴ! በእራት ግብዣችሁ ላይ ቀድሜ ነበር የተገኘሁት፤ ነገር ግን ገፍተራችሁ አባረራችሁኝ›› አለ፡፡ ሙሴም እኛ ያባረርነው ቡትቶ የለበሰ ደሀ ሽማግሌ ነው፡፡ ሽማግሌስ ማን ፈጠረው? ሙሴም ‹‹አንተ ነህ ጌታ ሆይ›› በማለት መለሰ፡፡ ይህን ጊዜ እግዚአብሔር ‹‹ታዲያ በፈጠርኩት ውስጥ መኖሬን ትጠራጠራለህ?›› አለው ሙሴም አላስተባበለም፡፡ እናማ ወዳጄ ይህ ሽማግሌ ላዩን ቢያስውብ፣ ልብስ ቢለበስና ቢያጌጥ ኖሮ ገፍትረው የሚያባርሩት ይመስልሃል? እኔም እልሃለሁ ጥሩ መጽሐፍ በጥሩ ሽፋኑ መለበጥ አለበት›› በከፊል ፈገግ ብሎ ተመለከተን፡፡

የመጀመሪያው ልጅም ‹‹እና የሰው ልጅ መመዘን ያለበት በአለባበሱ ነው እያልከኝ ነው?›› በማለት ቆጣ ብሎ ጠየቀ፡፡ ሁለተኛው ልጅም እኔ ማለት የፈለግኩት አለባበስ የሰው ልጅ መለኪያ መሆን አለበት ሳይሆን በዚህ ዘመን አለባበስን የውበት እና የስዕብና መለኪያ አድርገነዋል እያልኩህ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከአፈጣጠራችን ተነስና ስናየው ስህተት ነው፡፡ መሆንም የለበትም፡፡ ነገር ግን የአለባበስ ባህላችንን ስንመዝነው አለባበስ ከውበት መለኪየነት ወጥቶ የስብዕና መመዘኛ እየሆነ ነው፡፡ አለባበሳችንን የውበት መለኪያ ነው ብለን ስናምን እና ልብስ እርቃንን መሸፈኛ፣ ሙቀት እና ቅዝቃዜን መከላከያ ብቻ ነው ብለን ካልን አምን ስለ ቀለሙ፣ ብርቅየነቱ(ፋሽንነት)፣ ጥራቱ እንጨነቃለን? ለምን ያገኘነውን ነገር በመልበስ እርቃናችንን አንሸፍንም? ለምን ከሰውነት ቅርፃችን ጋር ተስማማ አልተስማማ እያልን መስታወት እናስቸግራለን? ዘመናዊ ላልናቸው አልባሳትስ ብዙ ብር አፍስሰን እንገዛ ነበርን? ስማህ አለባበስ የውበት መለኪያ ያልነበረው የሰው ልጅ ቅጠል በሚያገለድምበት ዘመን ይመስለኛል፡፡ በእርግጥ ከዘመን ዘመን የልብስ ትርጉም ተለዋውጧል፡፡ ድሮ ልብስ የእርቃን መሸፈኛ ብቻ የነበረ ቢሆንም አሁን አሁን ግን ልብስን የውበት ብቻ ሳይሆን የስብዕና መገለጫ እያደረግነው ነው፡፡ ይህን ስልህ የስብዕና መገለጫ እየሆነ መምጣቱን ለማስገንዘብ እንጂ ስብዕናችን በልብስ መለካቱ ያንገበግበናል፡፡ የውበት መገለጫ መሆኑ ግን አግባብ ነው እላለሁ፡፡ ለፎቶ ፍሬም እናደርግለት የለ፤ የፎቶ ፍሬም እኮ ለፎቶው ከአቧራ ብቻ የሚከላከል ሳይሆን ፎቶውን በመንከባከብ ውበት የሚጨምር በመሆኑ ነው፡፡ ከአቧራ እና እርጥበት ብቻ ቢሆን ኖሮ ፍሬም ማማረጥ ሳያስፈልግ በላስቲክ ብቻ እንሸፍነው ነበር፡፡ ስለዚህ ለገላችንም ጥሩ ፍሬም(ልብስ) ገዝተን ብናስውበው የተሰጠንን መንከባከብ ስለሆነ አግባብ ነው እልሃለሁ፡፡

እኔም ጣልቃ በመግባት ‹‹ወንድሜ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ? አብረህ ብታብራራልኝ›› እሱም ፈቃደኛ መሆኑን ጭንቅላቱን ከላይ ወደታች ወዝውዞ ገለፆልኝ ተመቻችቶ ተቀመጠ፡፡ ጆሮ እንደሰጠኝ ሳረጋግጥ ‹‹ለመሆኑ ስለ አለባበሳቸው አብዝተው የሚጨነቁ ሰዎች በራስ የመተማመን ስሜታቸው ምን ይመስል ይሆን?›› አልኩት፡፡ ለጥቂት ሰከንድ አሰላስሎ ፈገግ አለና ‹‹በራስ የመተማመን ስሜት እኮ አንጻራዊ እና ለመለካት አስቸጋሪ የሆነ ስሜት ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ስለአለባበሳቸው አብዝተው የሚጨነቁ እና የሌሎች ትኩረት ለመሳብ የሚጣጣሩ ሶዎችን የስነ-ልቦና ጠቢባኑ የስብዕና መመሳቃቀል (ቀውስ) የሆነው ልታይ ልታይ ባይነት የገጣማቸው እንደሚሆኑ ይስማማሉ፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ዋነው አላማቸው የሰዎችን ትኩረት አብዝተው ለመማረክ በመሆኑ ሰዎች ይህን ትኩረት አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ስነልቦናቸውንና ራሳቸውን ከንቱ አድርገው የማሰብ አባዜ ይጠናወታቸዋል፡፡ ወዳጄ እንዲህ አይነት ባህርይ ያለባቸው ሰዎች እኮ ውስጣቸው ያለውን የበዛ ክፍተት በሚታየው አብዝቶ መሽቀርቀር የበላይነትን ለማግኘት እየተጣጣሩ ነው፡፡ እንደ እነዚህ አይነት ሰዎች ውስጣቸው ከሚነግራቸው እውነት ይልቅ የሌሎች አስተያየት እውነትነት ስለሚገዝፍባቸው ትንሽ አድናቆት ሲያስፈነጥዛቸው ትንሽ ወቀሳም ያደማቸዋል፡፡ ይህን ስል የሰዎች አስተያይ አቀባበላችን እንጂ ጠቃሚም ጎጅም የሚያደርገው አስፈላጊ እንደሆነ ግን አስገንዝብሃለሁ፡፡ በተመስጠ እንደማደምጠው ሲያረጋግጥ በእርግጥ አንድ ሰው ስለአለባበሱ በመጠኑ ቢጠበብ ጤናማ ነው፡፡ ነገር ግን የቆሸሸ እና የተቀደደ እየለበሱ ለአለባበሱ የማይጨነቁ ከዛ ያለፈ የህይወት ግብ ስላለው (ላት) በሚባልላቸውም አልስማማም፡፡ ምክንያቱም አለባበሳችን በከፊልም ቢሆን ስለራሳችን ያለንን ስሜት ያንፀባርቃልና፡፡ ስለዚህ ከመጠን በላይ መጨነቅም ከስብዕና ቀውስ የሚመነጭ፣ ፈፅሞ አለመጨነቅም ከአሉታዊ ስሜት (ጭንቀት፣ ድብርት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ከማህበረሰቡ ባህሪ ማፈንገጥ ስሜት ወዘተ) የመነጨ ነው እላለሁ፡፡ ይህ ትንታኔ የሚሠራው ግን የቀወስ ድህነትን ግምት ውስጥ ሳያስገባ ነው፡፡›› በማለት ወራጅ ብሎ ተሰነባበትን ሁለቱም ወረዱ፡፡ እኔም እዚህ ጋ ልውረድላችሁ፡፡ ዳግም እንገናኝ፡፡

ሙገሳንም ሆነ ወቀሳን ለማስተናገድ ዝግጁ ነኝ! ስልክ ቁጥር፡ 0910818783

# የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ2007 ዓ.ም ምርጥ ተመራማሪዎች


አቶ ባዬህ አበራ

አቶ ባዬህ አበራ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ሲሆኑ በ2007 ዓ.ም 15 ችግር ፈች የምርምር ሥራዎቻቸውን በማሳተም በዩኒቨርሲቲው ካሉት ተመራማሪዎች ግንባር ቀደም በመሆን የዩኒቨርሲቲው የ2007 ዓ.ም ምርጥ ተማራማሪ ሆነዋል፡፡

ዶ/ር እንየዉ አድጎ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በግብርና እና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ሲሆኑ በ2007 ዓ.ም 13 ችግር ፈች የምርምር ሥራዎቻቸውን በማሳተም በዩኒቨርሲቲው ካሉት ተመራማሪዎች ግንባር ቀደም በመሆን የዩኒቨርሲቲው የ2007 ዓ.ም ምርጥ ተማራማሪ ሆነዋል፡፡


እንየዉ አድጎ (ዶ/ር)


አቶ ወንድምዓገኝ ሙሉ

አቶ ወንድምዓገኝ ሙሉ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ሲሆኑ በ2007 ዓ.ም 10 ችግር ፈች የምርምር ሥራዎቻቸውን በማሳተም በዩኒቨርሲቲው ካሉት ተመራማሪዎች ግንባር ቀደም በመሆን የዩኒቨርሲቲው የ2007 ዓ.ም ምርጥ ተማራማሪ ሆነዋል፡፡

## Entrepreneurship Development and Incubation Center

Bahir Dar University is striving to be one of the ten premier research universities in Africa by 2025. To realize this vision, the university has taken measures in establishing research centers and institutions. As part of this endeavor, among other Research Centers, Bahir Dar University Entrepreneurship Development and Incubation Center (EDIC) has been established in 2007. The center is so crucial since growth and development will be true when innovation is encouraged and conducive environment is created. Innovation by itself is not an end for growth and development. Rather the innovative ideas need to be transformed to commercialized business. The University community including the students, the faculty and the alumni can have innovative ideas that can be a vibrant business.

The student project work, the faculty research output, and the different creative ideas need to be incubated and commercialized. This will contribute a lot in job creation through modern business. It is evidenced in many researches that the innovative products that we see today in the market were an idea in universities some time ago. Hence, Bahir Dar University Entrepreneurship Development and Incubation Center (EDIC) has been established with the following vision and mission:

**Vision of the Center:** To be a leading centre for transforming knowledge and technology based ideas into vibrant business enterprises

**Mission of the center:** Strive to create a sustainable entrepreneurship ecosystem that will foster and support innovation and knowledge based entrepreneurship amongst the student , staff and community leading to the creation of jobs, wealth and social value through successful ventures.

With these vision and mission in mind the center has started its operation at small scale in 2007 in providing training for graduating class, mentoring student business ideas, consulting few university projects , organizing the office, preparing center establishing documents and plans.

The center has a Director and team of experts who work within and it will staff the required personnel soon. It has got budget from the university and planned to undertake many diversified activities in 2008. The center hopes to be successful with the opportunity having at hand which is the high university top management commitment and the government in general.

Therefore, we welcome you all to our office to work together on entrepreneurial agenda

Our Address: Wisdom Tower

4th floor, office No. G4-03

# FRESH Students' Welcoming Ceremony of 2008 E.C. Academic Year held at BDU, Sports Academy Stadium (photo gallery)













ነህ ማተሚያ ቤት ታተመ